# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 82ኛ ዓመት ቁጥር 004 መስከረም 4 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በኬንያው ፕሬዚዳንት በዓለ ሲመት ላይ ተገኝተዋል

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በትናንትናው ዕለት በአዲሱ የኬንያ ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ በዓለ ሲመት ላይ ታድመዋል።

ቀደም ሲል በኬንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ባጫ ደበሌ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድን ለኬንያው አዲሱ ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ያስተላለፉትን መልዕክት ማድረሳቸውን ማሳወቃቸው ይታወሳል።

አምባሳደሩ ኢትዮጵያ እና ኬንያ በልማት፣ ቀጣናዊ ሠላም እና ፀጥታ በማስፈን እንዲሁም በኢኮኖሚያዊ ትሥሥር ተቀራርበው መሥራታቸውን እንደሚቀጥሉ በትዊተር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት አስታውቀዋል።

ዊልያም ሩቶ ትናንት በካሳራኒ ስታዲየም በሚገኘው የበዓለ ሲመታቸው ሥነ ሥርዓት ላይ ቃለ መሓላ ፈጸመዋል።











ፎቶ- ገባቦ ገብሬ

## «አሸባሪው ትህነግ ጠላት ካልፈጠርኩ ሕልውናዬ አይቆይም የሚል አስተሳሰብ የተጠናወተው ነው»

ሲሳይ መንግስቱ(ዶ/ር)


ገጽ 4


## «የፀጥታው ምክር ቤት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ላይ የመሰብሰብ ስልጣን የለውም»

አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ

**አብዱረዛቅ መሐመድ**




<u>አዲስ አበባ</u>፡- የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ላይ ስብሰባ የመጥራት ህጋዊ ስልጣን የለውም ሲሉ በድርጅቱ የኢትዮጵያ ቋሚ መልእክተኛ አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ተናገሩ።

አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ለአንድ የአገር ውስጥ ሚድያ እንደተናገሩት፣ አሁን ላይ በኢትዮጵያ የተፈጠረው ችግር የውስጥ ጉዳይ ነው፡፡ አገራት ደግሞ ውስጥ ጉዳዮቻቸውን በራሳቸው የመፍታት ሉኣላዊነት


"የፀጥታው ምክር ቤት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## በአሸባሪው ትህነግ 11 ቤተሰቦቻቸውን የተነጠቁት አዛውንት


**ሞገስ ተስፋ**

አቶ ንጉሴ ደምሰው ከሽብር ቡድኑ ለመራቅ ከጎንደር መተማ፣ ከዚያም አዲስ አበባ፣ ከአዲስ አበባ ዲማ፣ ተመልሰው ትግራይ ያልሄዱበት የኢትዮጵያ ጫፍ የለም:: ሰላም ወርዷል ብለው ሁመራ ሲገቡ መጣ ብለው በድጋሜ ለዘጠኝ ወራት ለእስር ተዳረጉ::

በወልቃይት ጠገዴ ምድር በሕወሓት ትህነግ ያልተፈጸመ ግፍ የለም:: ከዛፍ እስከ ቁም እንስሳት ዘረፋ ተፈጽሞበታል:: የነቁና የበቁ ናቸው የተባሉ የወልቃይት ጠገዴ ነዋሪዎች በግፍ ታስረው እንዲሰወሩ ሲደረጉ


በአሸባሪው... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ- ገባቦ ገብሬ



አቶ ንጉሤ ደምሰው






## በኢፕድ ዘገባ - የታበሰ እንባ


ገጽ 6



# «የጠላትን ከንቱ ምኞት ማክሸፋችንን እንቀጥላለን»

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የጠላትን ከንቱ ምኞት ማክሸፋችንን ልንቀጥል ይገባል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ አሳሰቡ፡፡ አዲስ አበባን እና የዙሪያዋን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ሰላማዊ እና የተረጋጋ የማድረግ የጋራ እንቅስቃሴ ሥራችንን አጠናክረን መቀጠል አለብን ብለዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ በከተማዋ በዓሉን አስታኮ የተለያዩ ወንጀሎችን በመፈፀም የከተማዋን ሰላም ለማወክ፣ የገበያ አቅርቦት እጥረት እንዲያጋጥም እና ይህን ተከትሎም ተገቢ ያልሆነ የዋጋ ንረትን በማስከተል ኅብረተሰቡን ውጥረት ውስጥ ለመከተት አቅደው ሲዘጋጁ እና ሲያስተባብሩ የነበሩ አካላት ነበሩ።

ይህን እኩይ ድርጊት በመከላከል በዓሉ በሰላምና በተረጋጋ መልኩ እንዲከበር ማድረግ መቻሉ የጠላት ከንቱ ምኞት ከሽፏል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ ይህንን ተግባር ልንቀጥል ይገባል ብለዋል።

ነዋሪዎች፣ የመንግሥት መዋቅር፣ በየአካባቢው የተደራጁ የሕዝባዊ ሰራዊት አባላት፣ የአዲስ አበባ፣ የፌዴራልና የኦሮሚያ ልዩ ዞን የፀጥታ አካላት፣ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ዘመን መለወጫ በዓል ከዋዜማው አንስቶ በሰላም ተጀምሮ እንዲጠናቀቅ ላበረከቱት አስተዋፅኦ ከንቲባ አዳነች ምስጋና አቅርበዋል።

ሆኖም፣ በሁሉም አካላት የጋራ እንቅስቃሴ በመክሸፉ በዓሉ ሰላማዊ ሆኖ ማለፍ ችሏል ያሉት ከንቲባዋ፣ «ከዚህ የምንማረው ለአንድነታችን መተባበራችን የአሸናፊነታችን ምስጢር መሆኑን ነው» ብለዋል።

አሁንም፣ ቀጣዮቹንም ጊዜያት በተለይም የተለያዩ ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ በዓላትን አከባበር ጨምሮ የተጀመረው ከተማዋና የዙርያዋን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ሰላማዊ እና የተረጋጋ የማድረግ የጋራ እንቅስቃሴ ሥራችንን አጠናክረን በመቀጠል የጠላትን ከንቱ ምኞት ማክሸፋችንን እንቀጥል ሲሉም ከንቲባ አዳነች አቤቤ ጥሪ አቅርበዋል።

# 28 ሚሊዮን አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፈንድ ይፋ ተደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- «ቅንጅት ለአፍሪካ የአረንጓዴ አብዮት» (አግራ) የተሰኘው ድርጅት አህጉሪቱ የራሷን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የምታደርገውን ጥረት ለመደገፍና በ15 የአፍሪካ አገራት ውስጥ 28 ሚሊዮን አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ 550 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚሆን የማስጀመሪያ ገንዘብ ይፋ አደረገ።

በቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ የቦርድ ሊቀመንበርነት የሚመራው «ቅንጅት ለአፍሪካ የአረንጓዴ አብዮት» (አግራ) የተሰኘው የበጎ አድራጎት ድርጅት ከትናንት ወዲያ ይፋ እንዳደረገው በ15 የአፍሪካ አገራት 28 ሚሊዮን አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ አቅዷል።

በአዲሱ ፖሊሲ መሠረት፣ ድርጅቱ የግብርና ምርታማነትን እና ገቢን ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ የቦርዱን ሊቀመንበር ጠቅሶ ዘ ኢስት አፍሪካ ዘግቧል።



**የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ**

ድርጅቱ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ዋነኛ ትኩረቱ የዘር አጠቃቀም ሥርዓትን በማሻሻል፣ የመንግሥት ተሳትፎን በማሳደግ፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት እና የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮችን በመቅረፍ ላይ እንደሚሠራም ነው የተገለፀው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ እና እንደ ማዳበሪያ ያሉ የግብርና ግብዓቶች ዋጋ መናርን ጨምሮ በቀጣናው ያሉ አነስተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ አርሶ አደሮች ወቅታዊውን የውጭ ጫና ተሸክመው እንደሚገኙም የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በብዙ ልፋት የተገኙ የግብርና ውጤቶች አሁን ላይ በውጫዊ ክስተቶች በተለይም በአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖ ምክንያት ስጋት ውስጥ በመሆናቸው ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ እንደሚገባ ነው የተጠቆመው።

የአግራ የቦርድ ሊቀመንበር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በምሥራቅ አፍሪካ በየወቅቱ የሚከሰተው ድርቅ እንዲሁም በደቡባዊ አፍሪካ የሚታየው ኃያል አውሎ ንፋስ አሉታዊ ተፅእኖ ማስከተላቸውን ገልጸዋል።

የአየር ሁኔታ እና የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮች እንዲሁ ከግብርና ግብዓቶች የዋጋ መናር ጋር ተዳምረው በግብርና ምርትና ምርታማነት ላይ እያስከተሉ ያሉት ተጽዕኖ በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነም መናገራቸውን ዘገባው ጠቁሟል።




# የግብርና ምርት አጋዥ መሣሪያዎችን የሚያመርት ፋብሪካ ተመረቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ቢሾፍቱ ከተማ በ133 ሚሊዮን ብር ካፒታል የተቋቋመውና የግብርና ምርት አጋዥ የሆኑ መሣሪያዎችን የሚያመርተው የጅብዱ ሞተርስ አክሲዮን ማኅበር ፋብሪካ ተመረቀ።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ እና የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴን ተገኝተዋል።

ፋብሪካው ለመስኖ ልማት የሚያግዙ የውሃ መሳቢያ (ፓምፕን) ጨምሮ ለግብርና ምርት አጋዥ የሆኑ የግብርና መሣሪያዎች ያመርታል ተብሏል፡፡

የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ በገጠር ልማት ዘርፍ አራት ዋና ግቦችን አቅዶ እየሠራ መሆኑን በዚህ ወቅት አስታውቋል።

ከፋብሪካው ምረቃ ሥነ ሥርዓት በኋላ የተለያየ መጠን ያላቸው 16 ሺህ 803 የውሃ መሳቢያ ፓምፖች ለአርሶ አደሮች ተከፋፍለዋል፡፡ የፋብሪካው ሥራ መጀመር የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራና ከውጭ የሚገቡ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት እንደሚያግዝ ተጠቁሟል።

ለተጠቃሚዎች የሚተላለፉት የውሃ መሳቢያ ሞተሮች (ፓምፖችም )75 ሺህ ሄክታር መሬት ለማልማት የሚያግዙ መሆናቸው ተጠቅሷል።

ኢትዮጵያ የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ሁለተናዊ ጥረት በማድረግ ላይ እያለች ሲሆን ይህ ፋብሪካ ሥራ መጀመሩ በበጋ መስኖ በቀላሉ ለማልማት አንድ ተጨማሪ አቅም እንደሚሆን ተገልጿል፡፡

# የሥራና ክሂሎት ሚኒስቴር እና የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በጋራ ለመሥራት ተስማሙ

ዋቅሹም ፍቃዱ



አዲስ አበባ፡- የሥራና ክሂሎት ሚኒስቴር እና የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በቅንጅት ለመሥራት የጋራ እቅድ ትግበራ ስምምነት ተፈራረሙ።

የሥራና ክሂሎት ሚኒስትሯ ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል በወቅቱ እንደተናገሩት፣ ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በተለያዩ የሥራ መስኮች በመሰማራት እንደ አገር የበርካቶችን ሕይወት በመቀየር ትልቅ አሻራ ያስቀመጠና እያስቀመጠ ያለ ድርጅት ነው።

የተደረገው ስምምነት ከእስካሁኑ የተሻለና በተቀናጀ መልኩ ለመሥራት የሚያስችል፣ ምናልባትም መሥሪያ ቤቱ ከሚድሮክ ጋር በመፈራረሙ የመጀመሪያና ለሌሎች አርአያ የሚሆን ነው ያሉት ሚኒስትሯ፣ የተደረገው ስምምነት ተግባራዊ ሆኖ ፍሬ እንደሚያፈራ የሚድሮክ ሥራ አመራሮችና የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቁርጠኝነትና ቁመና የተሻለ ደረጃ ላይ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ባለፉት ጥቂት ወራት ከሁለቱ ተቋማት የተውጣጡ ሙያተኞችና የሥራ አመራሮች በጋራ ለመሥራት የሚያስችሉ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማድረጋቸውን የጠቆሙት ወ/ሮ ሙፈሪያት፣ ጠቃሚና ተግባራዊ የሚደረጉ መስኮች ላይ በጋራ ለመሥራት የጋራ እቅድ ላይ መስማማታቸውን ተናግረዋል፡፡

እንደ ወ/ሮ ሙፈሪያት ማብራሪያ፣ ከሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ጋር በመሆን የሥራ እድል ከመፍጠር በዘለለ የባህሪ ለውጥና የሥራ ፈጠራ ክሂሎት እንዲዳብር በትኩረት ይሠራል፡፡

በስምምነቱ መሠረት የሥራና ክሂሎት ሚኒስቴር በኢንዱስትር ዘርፍ የሚፈለገውን ብቃትና ክሂሎት ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማቅረብ ባሻገር የሥራ እድል ለተፈጠረላቸው ባለሙያዎች የሥራ ላይ ሥልጠና ያዘጋጃል ያሉት ሚኒስትሯ፣ መንግሥት ለግሉ ዘርፍ በሰጠው ትኩረት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሥራ ላይ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ባረጋገጠ መልኩ በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በቱሪዝም፣ በኮንስትራክሽንና በማዕድን የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በማብቃት ለሚድሮክ በስፋት በማቅረብ ድርጅቱንም እየጠቀመ ለብዙዎች የሥራ እድል እንደሚፈጠር ሙሉ እምነት እንዳላቸው ተናግረዋል።

የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጀማል አህመድ በበኩላቸው ድርጅታቸው በስድስት የሥራ ዘርፍ የተሰማራ ወደ 50 የሚጠጉ ኩባንያዎች ያሉትና ለ64 ሺህ ዜጎች የሥራ እድል የፈጠረ ግዙፍ ድርጅት መሆኑን ጠቅሰው፣ ድርጅቱ ከአገሪቱ ለውጥ ጋር ራሱን እንደገና አደራጅቶ ለበለጠ ውጤታማነት እየተጋ ባለበት ወቅት ስምምነቱን መፈራረሙ መልካም አጋጣሚ ነው ብለዋል፡፡

ድርጅቱ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች በመሰማራት በአገሪቱ እድገት ውስጥ የራሱ ሚና መጫወቱ እንዳለ ሆኖ በቢዝነስ መስኮች የተሰማራ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ለተሻለ ውጤታማነት ብቁ የሰው ኃይል ወሳኝ መሆኑን ገልጸው፣ ያሉትን የክሂሎትና የሥራ አመራር ክፍተቶችን ለመድፈን ስምምነቱ ጠቃሚ መሆኑን ተናግረዋል።

ድርጅቱ ያለውን አቅም ተጠቅሞ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማስፋፋት ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል እንደሚፈጠርም አክለው አመልክተዋል፡፡

# በአምስት ወራት ከ22ሺህ በላይ ይዞታዎች ወሰን ተካለሉ

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ መሬት ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ባለፉት አምስት ወራት ውስጥ 22ሺህ 339 ይዞታዎችን የወሰን ማካለልና ቅየሳ ማከናወኑን አስታወቀ፡፡

የኤጀንሲው የይዞታ ማረጋገጥና አድራሻ ዝርጋታ ሥርዓት ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ጀማል ሃጂ ኤጀንሲው ለአምስት ወራት ሲያከናውን የቆየው ይዞታን በመስክ እና በሰነድ የማረጋገጡ ሥራን አስመልክተው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ ለተከታታይ አምስት ወራት በስልታዊ ወይም በመደዳ የማረጋገጥ ዘዴ እስከ ጳጉሜ አምስት ቀን 2014 ዓ.ም መካሄዱን ጠቅሰዋል፡፡

የሕዝብ ታዛቢዎች በተገኙበት 22ሺህ 339 ይዞታዎችን የወሰን ማካለልና የቅየሳ ሥራ ተከናውኗል ያሉት ኃላፊው፤ ይህም የእቅዱን መቶ በመቶ ያሳካ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

የሕዝብ ታዛቢዎች ከቀጣና መክፈቻ አንስቶ እስከ ቀጣና መዝጊያው ፕሮግራም ድረስ ሥራውን ሲያስተባብሩ፣ ሲታዘቡ መቆየታቸውን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል፡፡ የሕዝብ ታዛቢዎች በተገኙበት 21ሺህ 436 ይዞታዎችን ለማካለል ታቅዶ 22ሺህ 339 ይዞታዎችን የወሰን ማካለልና የቅየሳ ሥራ መከናወኑን ይህም የእቅዱን መቶ በመቶ መፈጸም እንዳስቻለ ገልጸዋል፡፡

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ የይዞታ ማረጋገጥ ሥራው የተሳካ እንዲሆን በአስሩም ክፍለ ከተማዎች ለ15ሺህ ባለይዞታዎች የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራው መካሄዱን ጠቅሰዋል፡፡ የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራው በሕዝብ ተሳትፎ የታጀበና የተሳካ ለማድረግ 125 የሕዝብ ታዛቢዎች እና 200 የቅሬታ ሰሚ ጉባኤ አባላት የማስመረጥ ሥራ ተካሂዶ ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለማስገንዘብ በአስሩ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ስልጠና መሰጠቱንም አንስተዋል፡፡ በዚህም የይረጋገጥልኝ ማመልከቻዎች በአግባቡ ተስተናግደዋል ነው ያሉት፡፡

የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ሥራው ጥራቱን ለማስጠበቅ በክትትልና ድጋፍ ባለሙያዎች ተገቢ የሆነ ድጋፍና እንዲያገኙ መደረጉንም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል፡፡



ኢንጂነር ጀማል ሃጂ

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ በሰነድና በመስክ ለማረጋገጥ በተሠራው ሥራ ከ22ሺህ 339 ይዞታዎች 10 ሺህ 401 ለምዝገባ ብቁ ሲሆኑ፤ 11ሺህ 938 ይዞታዎች የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች ሰነዶችን በጊዜ ባለማስረከባቸው፣ መብት ያልተፈጠረላቸውና በሙብለጥና በማነስ ተመላሽ ሆኖ ያልተስተካከሉ በመሆናቸው ወደ ክርክር መዝገብ ሊገቡ ችለዋል፡፡

በቀጣይ ብቁ የሆኑ ይዞታዎች በካዳስተር ሲስተሙ እንደሚመዘገቡ ጠቅሰው፤ ባለይዞታዎች በእጃቸው ያለውን ሰርተፊኬት በአካል ቀርበው በመመለስ አዲሱን ዲጂታል ሰርተፊኬት በ30 ቀናት ውስጥ መውሰድ ይኖርባቸዋል ብለዋል። የስም ዝውውርና የሙብት፣ ክልከላና ኃላፊነቶች እግድ ተነስቶ አገልግሎቱ እንደሚቀጥልም አመላክተዋል፡፡ ብቁ ያልሆኑ የይዞታ መዝገቦች ክርክር ውስጥ ስለገቡ ከክርክር መዝገብ እስኪወጡ የስም ዝውውርና የሙብት፣ ክልከላና ኃላፊነቶች እግድም እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

ከክርክር ለማውጣት በየከፍለ ከተማ ያሉ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች፤ ርክክብ ያልተደረገባቸውን ሁለት ሺህ 619 ሰነዶችን በአጭር ጊዜ ወደኤጀንሲው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በመላክ፤ በተለያየ ምክንያት ልዩነት ለተፈጠረባቸው ሰባት ሺህ 225 አስቸኳይ ምላሽ በመስጠት፤ መብት ያልተፈጠረላቸውን ሦስት ሺህ 395 መዝገቦችን መብት በመፍጠር የካዳስተር ግንባታ ሥርዓቱ እንዲፋጠንና የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት የራሳቸውን ወሳኝ ሚና እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡ ባለይዞታዎቹም በመሬት ልማትና አስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች በመቅረብ የሚጠበቅባቸውን እንዲያሟሉ ጠይቀዋል፡፡



# የኮሚሽኑ ሠራተኞች ለጥምር ጦሩ ደም ለገሱ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞችና አመራሮች ለጥምር ጦሩ ደም ለግሰዋል።

የሲቪል ሰርቪስ የኮሚሽን ኮሚሽነር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አልማው መንግሥት እንደገለጹት፤ የደም ልገሳው ፕሮግራም ያስፈለገው ሕወሓት በጀመረው ጦርነት ምክንያት የአገር ድንበር ለሚጠብቁ የመከላከያ ሰራዊት ድጋፍ ለማድረግ ነው። በጦርነት ወቅት መቁሰልና ደም መፍሰስ ስለሚኖር በደም እጥረት ምክንያት አንድም ወታደር እንዳይሞት ሠራተኞችና አመራሮች የደም ልገሳ ፕሮግራም ማዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

ቀደም ሲል ለጥምር ጦሩ በጥሬ ገንዘብ ወደ ሁለት ሚሊዮን ብር ድጋፍ መደረጉን የገለጹት ኃላፊው፤ ከሥራ አመራር ኢንስቲትዩቱት ጋር በመሆን የሁለት ሚሊዮን ብር ቁሳቁስ ድጋፍ ለማድረግ በዝግጅት ላይ እንገኛለን ብለዋል። ከደም ልገሳው በተጨማሪ በድምሩ 4 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ድጋፍ ስለመደረጉም ገልጸዋል። ኮሚሽኑ ወደፊትም አስፈላጊ ድጋፎችን ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን አረጋግጠዋል።

በጦርነት የተፈታ ችግር የለም ያሉት ኃላፊው፤ ጦርነት የሰው ሕይወት ያጠፋል፣ ንብረት ያወድማል። የመንግሥት ተቀዳሚ ፍላጎትም ጦርነቱ በሰላም እንዲቋጭ ነው። ነገር ግን ሕወሓት ሰላም ፈላጊ ቡድን ባለመሆኑና መንግሥት የአገርን ዳር ድንበር የማስከበር ግዴታ ስላለበት ሰራዊቱ የሚያደርገውን ተጋድሎ መደገፍ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው ብለዋል።

የተቋሙ ሠራተኛ ሰላማዊት ኃይሌ እንደገለጸችው፤ ለሰራዊቱ ደም መለገስ ጥቂቱ ስጦታ ነው። አገራችን ሰላም እንድትሆን ኅብረተሰቡ የአካባቢውን ሰላም በጋራ መጠበቅ አለበት። መንግሥትም አሸባሪን የሕወሓት ቡድን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በመደምሰስ አገሪቷን ወደ ሰላም ማምጣት አለበት።

ሁሉም ዜጋ በያዘው ሥራ ኃላፊነቱን በአግባቡ በመወጣት የኢትዮጵያን ልማት ማፋጠን ይኖርበታል ያለችው ሰላማዊት፤ በተለይ ወጣቱ ለሰራዊቱ ደም እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ ሕይወቱን ለሚሰጠው ሰራዊት ደሙን መለገስ እንዳለበት አሳስባለች።

በኮሚሽኑ የክልሎች ድጋፍ ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ግዛቸው መኩሪያ በበኩላቸው፤ መከላከያው ከሚሠራው ሥራ አንጻር በሳምንትና በወር ውስጥ ሊተካ የሚችለውን ደም መለገስ በጣም ትንሹ ተግባር ነው። ሁሉም ዜጋ መኖር፣ መሥራትና መለወጥ የሚችለው አገር ሰላም ስትሆን መሆኑን ተገንዝቦ የአገርን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ ለሚታገለው ሰራዊት የሚቻለውን ሁሉ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል። ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠልና ከደም መለገስ በተጨማሪ እስከ ግንባር ድረስ በመሄድ ማበረታታት ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ በአሸባሪው ቡድን ለዘመናት ከፍተኛ ፈተና ደርሶባታል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በአንደኛና በሁለተኛው ዙር በከፈተው ጦርነት በአማራና በአፋር ክልሎች በርካታ የመንግሥትና የግለሰብ ተቋማትን አውድሟል። ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል። መንግሥት የወደሙ ተቋማትን ለመገንባት ደፋ ቀና በሚልበት ወቅት ዳግም ውድመት ለመፈጸም ሦስተኛ ዙር ጦርነት የከፈተ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ በጋራ በመሆን የመመከት ኃላፊነት እንዳለበት አሳስበዋል።

# የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ከዳር ለማድረስ አገራዊ አንድነትን ማጠናከር ይገባል

**ሙሳ ሙሐመድ**




ፎቶ - በሃይሉ አብርሃ

አዲስ አበባ፡- በሁሉም ዘርፍ የተጀመሩ አገራዊ ሥራዎችን ከዳር ለማድረስ አገራዊ አንድነትን በማጠናከር በጋራ መሥራት እንደሚገባ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት አንደኛ መደበኛ ጉባኤ ትናንት ሲካሄድ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሓጂ ኢብራሒም ቱፋ እንደተናገሩት፣ በኢትዮጵያ የእምነትና አገራዊ አንድነትን ማጠናከር ከእያንዳንዱ አማኝ እና ዜጋ ይጠበቀባቸዋል፡፡ እምነትና አገራዊ አንድነትን ማጠናከር በሁሉም ዘርፍ የተጀመሩ ጅምር አገራዊ ሥራዎችን ከዳር ለማድረስ ያስችለናል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያውያንና የእስልምና አማኞች አንድነታችን ተጠናክሮ በማየቴ አሁን ላይ ለመኖር ጓጉቻለሁ ያሉት ሼህ ሓጂ ኢብራሒም፣ የእስልም እምነት አስተምሮ አንድነትን ማጠናከርንና ለአገራዊ ሥራዎች በጋራ መቆምን ያበረታታል ብለዋል፡፡

አንድነታችንን ሲጠናከርና አብረን ስንታይ ልማቶቻችንና ማደጋችንን ማየት የማይፈልጉ ሁሉ ይደነግጣሉ ያሉት ሼህ ሓጂ ኢብራሒም፣ በዚያው ልክ ወዳጆቻችን ይደሰታሉ፤ ልማታችንንም ለመደገፍ ይነሳሳሉ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በአማኞች ዘንድ መለያየት አያምርብንም ያሉት ሼህ ሓጂ ኢብራሒም፣ በጋራ ማበብ፣ መፍካትና መድመቅ የምንችለው በአማኞችና ዜጎች መካከል ብቻ ሳይሆን በሰዎች መካከልም ስንዋደድና አንድነታችን ስናጠናክር ነው ብለዋል፡፡

በአገራችን የመጣውን ችግር ሁሉ አብረን መሸከምና መሻገር አለብን ሲሉ የተናገሩት ሼህ ሓጂ ኢብራሒም፣ በእምነታችንም በኩል አንድነታችንን አጠናክረን የአገራችንን ልማትና ልምላሜ ማፋጠን ይጠበቅብናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ሼህ ሓጂ ኢብራሒም ገለጻ፣ ወቅቱ መከፋፈልንና መንለያየትን አይፈልም፡፡ ይልቁንም ከመቼውም ጊዜ በላይ በአንድነት መቆምን የሚጠይቅ ነውና አብረን በሁሉም ጉዳዮቻችን ልንቆም ይገባናል ሲሉም መክረዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ፣ ለአማኞች ከልባችሁ ተቀራርባችሁና እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ የእምነቱንና የአገሪቱን ክብር ማስቀጠል ይጠበቅባችኋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

«መሪዎች ሰዎች ነን፤ እንሳሳታለን፤ እምነቱንና አገሪቱን ለማገልገል እስከመረጣችሁን ድረስ ስንሳሳት ንገሩን፤ መልሱን፣ እምነቱንና አገሪቱን ለማገልገል ነው የቆምነው»ብለዋል፡፡

የእምነት ተቋማት በአንድነት፤ በመቻቻል፤ በመፈቃቀር፣ በልማት ሥራዎች ሁሉ የኢትዮጵያና የአፍሪካ ተምሳሌት መሆን ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሸህ ሓጂ ሱለጧን ሐጂ አማን በበኩላቸው፣ በእምነትና በአገራዊ ጉዳዮች ላይ አንድነታችንና ኅብረታችን መጠናከር አለበት፤ የአገራችንና የዓለም ወቅታዊ ሁኔታ ይህን ይሻል ብለዋል፡፡የልማትና ሰላም ሥራዎችን ለማስቀጠል አንድነታችን እንደ ድንጋይ የጠጠረና እንደ ብረት የጠነከር ሊሆን ይገባል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ለለውጥ የተከፈቱትን መንገዶች መከተልና ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ማድረግ ደግሞ በእምነቱ አማኞች ዘንድ ግዴታ መሆኑን ተናግረው፣ በአገራችንና በእስልምና ኃይማኖት የመከፋፈልና የመገፋፋት መንገዱ ተዘግቷል፤ ለሁላችንም ኢትዮጵያውያን የአብሮነትና ልማት ጎዳና ደግሞ ተከፍቷል ብለዋል፡፡

በተከፈተው የሰላምና የልማት ጎዳና አንድነታችንን አጠናክረን መቀጠል ያሻናልና እንቀጥል ሲሉ ለምዕመናኑና ለመላ ኢትዮጵያውያን ጥሪ አቅርበዋል፡፡



# «አሸባሪው ትህነግ ጠላት ካልፈጠርኩ ሕልውናዬ አይቆይም የሚል አስተሳሰብ የተጠናወተው ነው»

**ሲሳይ መንግስቴ(ዶ/ር)**

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ :- አሸባሪው ትህነግ ጠላት ካልፈጠርኩ ሕልውናዬ አይቆይም የሚል አስተሳሰብ የተጠናወተው ጸረ ሕዝብ ቡድን መሆኑንና የአማራን ሕዝብ የሚያፈናቅለው፣ የሚገድለውና ግፍ የሚፈጽመው በጥላቻ ህልውናውን ለማቆየት ከመፈለግ መሆኑን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰብዓዊ መብትና የፌዴራሊዝም መምህር ሲሳይ መንግስቴ (ዶ/ር) ገለጹ።

ዶክተር ሲሳይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሰሞኑን ከትህነግ ማዕከላዊ ኮሚቴ አፈትልኮ የወጣው ምስጢራዊ ሰነድ ቡድኑ ጠላት እስካልፈጠረ ድረስ ሕልውናዬም አይቆይም የሚል አስተሳሰብ የተጠናወተውና የቆየ የበታችነት በሽታ ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው።

አሸባሪው ትህነግ የአማራ ሕዝብን አምርሮ ይጠላል። ደጋፊው የሆኑ የትግራይ ልሂቃንም በአማራ ሕዝብ ላይ ያላቸውን ጥላቻ በተለያየ ጊዜ ሲገልጹ ታይተዋልም ነው ያሉት።

ቡድኑ በ1968 ዓ.ም ባወጣው የፖለቲካ ማኒፌስቶ አማራን ግንባር ቀደም ጠላት ማድረጉንና ማኅበራዊ ዕረፍት እንነሳዋለን ብሎ የተነሳ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በዚህም የጥላቻ መንገዱ ቡድኑ ባለፉት 47 ዓመታት አማራን ማኅበራዊ ዕረፍት ሲነሳ ኖሯል። የትህነግ የኪነት ቡድን በሚዘፍናቸው፣ በሚያዘጋጃቸው መደበኛ ድራማዎችና ሙዚቃዊ ተውኔቶችም ሳይቀር የአማራ ሕዝብ ጠላት ነው፤ «አሳደህ ምታው ያንን አማራ» እያለ ሲዘፍንና ሲቀሰቅስ ኖሯል ብለዋል።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ የአማራ እና የትግራይ ሕዝቦች በቋንቋ ይለያዩ እንጂ፤ ተመሳሳይ ታሪክ፣ ባህል እና ሃይማኖት ያላቸው ናቸው። ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያን በጋራ እየገነቡ እና እያጸኑ ነው የኖሩት።

በመካከላቸው የተለየ ባህልና ታሪክ የለም። አንዱ የሌላውን ታሪክና ባህል የሚሰርቅበት ዕድልም የለውም። ነገር ግን ቡድኑ የትግራይን ሕዝብ ለማነሳሳት እና ከጎኑ ለማሰለፍ ስለፈለገ ጠላት እንደሆነ አድርጎ ጥላቻ ትርክት ፈጥሮ ቀንና ሌሊት ይሠራል።

ዶክተር ሲሳይ እንዳሉት የትህነግ መሪዎች የአማራ ገዢ መደብ ብለው አማራ የበላይነቱን ይዞ የኖረባት አገር እና በአማራ አምሳያ የተቀረጸች ኢትዮጵያ ናት ብለው ያስባሉ። ባለፉት 27 ዓመታት እነርሱ በትግራይ አምሳያ የተቀረጸች ኢትዮጵያን ለማምጣት ሲሞክሩ እንደነበር ግን ይታወቃል ብለዋል።

ቡድኑ በሰነዱ «የማጠቃለያ ምዕራፍ አካሄድና ስትራቴጂ» በሚል የነደፈው ስትራቴጂ፤ አካሄዱን የነደፈበት ነው። ማጥቃት ከመጀመሩ በፊትም መስከረም 2013 ዓ.ም ጽፎ ባሰራጨው ስትራቴጂ የዐቢይን (ዶክተር) አስተዳደር አስወግዶ ኢትዮጵያን መልሶ መቆጣጠር እንደሚችል፣ የትግራይን አገር የመመስረት ማሳየቱን ነው ያስታወሱት።

## «የፀጥታው ምክር ቤት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አላቸው፡፡ ሆኖም ጉዳዩ ዓለም አቀፍ የጸጥታና ደኅንነት ስጋት እስካልሆነ ድረስ የመንግሥታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ጉዳዩን አጀንዳ አድርጎ ስብሰባ የመጥራት ህጋዊ ስልጣን የለውም።

የኢትዮጵያን ጉዳይ ዓለም አቀፍ የጸጥታና ደኅንነት ስጋት ይሆናል በሚል አንዳንድ አገራት ጉዳዩን ከራሳቸው ፍላጎት አንጻር በማየት የሽብርተኛው የሕወሓት ቡድንን ጉዳይ ይዘው ወደ ጸጥታው ምክር ቤት መሄድ ሥራቸው አድርገውታል ያሉት አምባሳደር ታዬ፤ የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ጉዳይን ሳይጨምር በኢትዮጵያ ካለው ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ብቻ ባለፉት ሁለት ዓመታት ምክር ቤቱ ለ12ኛ ጊዜ ስብሰባ መጥራቱን አስረድተዋል።

እንደ ቋሚ መልዕክተኛው ገለጻ፣ ምክር ቤቱ በሰሜኑ አገራችን ከተከሰተው ጦርነት ጋር በተያያዘ ሁለት ጊዜም መግለጫ ሰጥቷል፤ ጉዳዩ ዓለም አቀፍ የጸጥታ አንድምታ በሌለበት ሁኔታ ምክር ቤቱ የአገራትን ጉዳይ የሚመለከትበት አንዳችም ምክንያት የለውም።

በአንድ አፍሪካዊ አገር ውስጥ ችግር አለ ተብሎ ከታሰበም ጉዳዩ መታየት ያለበት በአፍሪካ ኅብረት በኩል መሆኑን ጠቁመው፤ በአፍሪካ ኅብረት የሰላምና ጸጥታ ምክር ቤትና በመንግሥታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በኩል ያለው ግንኙነት የሚወሰነውም በዚሁ መርህ መሆኑን ገልጸዋል።

አንዳንድ አባል አገራት ካላቸው ፍላጎት አንጻር በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ስብሰባ እንዲጠራ ሊያደርጉ እንደሚችሉ የጠቆሙት ቋሚ መልዕክተኛው፤ «ስብሰባ ከጠሩም ውሳኔዎች እንዳይተላለፉና መግለጫዎች እንዳይሰጡ በማድረግ ስብሰባው ውጤት አልባ ለማድረግ በኢትዮጵያ በኩል እየተሠራ ነው» ሲሉም አብራርተዋል።

ይህን ለማድረግ የሁሉም አባል አገራት ስምምነት እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ «የኢትዮጵያ የውስጥ ችግሮች በራሷ መፈታት አለባቸው» የሚል አቋም የያዙና ወሳኝ ድምጽ ያላቸው በርካታ አገራት እንዳሉም ጠቁመዋል።

ሽብርተኛው የሕወሓት ቡድን ለመንግሥታቱ ድርጅት የላካቸው ደብዳቤዎችን በተመለከተ፣ የሽብር ቡድኑ ከመርህ ባፈነገጠ መልኩ ለስድስተኛ ጊዜ ለድርጅቱ ደብዳቤ መላኩን የተናገሩት ቋሚ መልዕክተኛው፤ ደብዳቤዎቹ እርስ በእርስ የሚጣረሱና ሃሳበ ጽኑነት የሌላቸው መሆናቸውንም አስረድተዋል።

መንግሥት ያልሆኑ አካላት የሚጽፏቸው ደብዳቤዎች በሙሉ የመንግሥታቱ ድርጅትን በር ያንኳኳሉ ማለት አይቻልም ያሉት አምባሳደር ታዬ፤ ነገር ግን በቀረቡ ደብዳቤዎች ሁሉ ስብሰባ አይጠራም ብለዋል።

የመንግሥታቱ ድርጅት የአባል አገራት ተቋም ሲሆን አገራቱ የሚስተናገዱትም በአሠራር፣ በደንቦችና በድርጅቱ ቻርተር መሠረት መሆኑንም አብራርተዋል።

## በአሸባሪው ትህነግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከእስርና ከሞት የተረፉት ደግሞ ቀየውን ለቆ እንዲሰደድ ተደርጓል። አንተ የመስፍን ልጅ፣ አንተ የአደሃሪ ልጅ እየተባሉ ብዙ ግፍ አይተዋል፤ ግፍ እና ስቃዩን ከማየት ሞት ይሻል ነበር ይላሉ።

በወልቃይት አዲረመጥ ወረዳ ደጀና ጭርቆስ ቀበሌ በ1953 ዓ.ም የተወለዱት አቶ ንጉሴ ደምሰው እንደሚሉት፤ የሽብር ቡድኑ የ1967 የትግል ማንፌስቶውን ሲቀርጽ አማራን ጠላቱ አድርጎ በመሳል ነው። አሸባሪው ትህነግ ወደ ወልቃይት ጠገዴ ሲገባ ጭፍጨፋውን የጀመረው ከቤተሰቦቻቸው መሆኑን ይናገራሉ። ታዋቂ፣ አስታራቂና ነገር አዋቂ የሆኑ ወልቃይቴ በሸብር ቡድኑ ጨለማ ውስጥ ይታሠራል፤ ይገረፋል፣ ስቃጥ በሆነ ሁኔታ ይገደላል። በተለይም መካሪ፣ ዘካሪና አስታራቂ የሆኑ ሽማግሌዎችን በግፍ ይረሽናል።

አዛውንቱ እንደሚሉት አሸባሪው ትህነግ በቅድሚያ የወልቃይትን ምድር ሲረግጥ ለማኅበረሰቡ ጥያቄ ሲያቀርብ ማኅበረሰቡ ምላሹ በሰላም መኖር ይቻላል የሚል ነበር፤ ነገር ግን መሣሪያ አውርዱ ካላችሁ አይሆንም የሚል ነበር። ይህን መልስ ከሰጡት መካከል ደግሞ የአቶ ንጉሴ ደምሰው አያት አቶ ልጃለም ታየ ነበሩ። ከዚያም «ይች ባቄላ ካደረች አትቆረጠም» ብለው በ1980 ወስደው በስውር ካሰሩ በኋላ ንብረታቸውን በሙሉ ዘርፈው በግፍ እንደረሸኗቸው ገልጸዋል።

ከእስርና ከሞት የተረፈው ቤተሰብ ወደ ጎረቤት አገር መሰደዱን የሚገልጹት አቶ ንጉሴ፤ 11 የቤተሰብ አባላቱን በግፍ በጨለማ በማጎር አሰቃይተው ገድለዋቸዋል ይላሉ። ከተገደሉት መካከል የእናታቸው ታናሽ ወንድ ያለም ታየ፣ የእናታቸው ሰገዱ ልጃለም ወንድሞች ተክሌ ልጃለም፣ ያለምእሸት ልጃለም፣ አዲሴ ልጃለም በግፍ የሞትን ጽዋ እንዲጠጡ ተደርጓል። ታናሽ ወንድማቸው ባህታህ ደምሰው፣ ያክስታቸው ልጅ ርስቀይ ታደሰ፣ ጥጋብነህ በርሄ፣ ደጀኑ ማሞ፣ ጢጋ ጥሩነህና አበራ ጥሩነህ ወንድማማቾች ግዛገም ውስጥ በግፍ መገደላቸውን ይገልጻሉ።

አቶ ንጉሴ ቤተሰቦቻቸው በግፍ ታስረው በተገደሉበት ግዛገም በተባለው ስውር እስር ቤት ከሦስት አመት በላይ ታስረው ሲሰቃዩ በተዓምር በሕይወት ተርፈው ለምስክርነት መብቃታቸውን ገልጸዋል። ቤተሰባቸውን በግፍ እንዲገደሉ ያደረጉበትን ምክንያት ሲገልጹ፤ ሕዝቡን አሳምጾው ወረራችንን እያደናቀፉብናል ብለው ቀድመው አስረው እንደገደሏቸው ተናግረዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን በእሳቸው መዝገብ ብቻ 400 የሚሆኑ አዛውንቶችና አረጋውያን በተወለዱበት አካባቢ ተገድለዋል።

ሰዎችን ከገደሉ በኋላ ቤተሰቦቻቸው ሲጠይቁ ሌላ አካባቢ ትምህርት እያስተማሩ ነው የሚል መልስ ይሰጡ እንደነበር የሚገልጹት አቶ ንጉሴ፤ ሕዝቡ አልቅሶ እንኳን እርሙን እንዳያወጣ ተደርጓል። ከሞት የተረፉበትን መንገድ ሲናገሩ ለእነሱ ታዛዥ በመሆን የእስር ቤት ጉድጓድ ቆፋሪ በመሆናቸው ነው። ከተራራ ስር ይቆፈራል ግድግዳ በእንጨት ይሠራበታል፤ ከላይ አፈር ይደፋበታል፣ ከዚያ ውስጡ ንጹሃን ገብተው መከራ ያዩበታል። በአንድ ጊዜ ብቻ 50 የሚደርስ ሰው ይገባል፤ ጠዋት ግን ሲታይ 10 የሚሆኑ ብቻ ይገኛሉ። ሌላው የት እንደወሰዱት አይታወቅም፤ ወስደው በማይታወቅ ጫካ ይረሽናሉ ብለዋል።

አቶ ንጉሴ ከአስከፊው ስቃይ ለማምለጥ ሲሉ ከጎንደር መተማ፣ ከዚያም አዲስ አበባ፣ ከአዲስ አበባ ዱማ፣ ተመልሰው ትግራይ ገቡ። በመጨረሻም ሰላም መጥቷል ብለው ሁመራ ሲገቡ መጣ ብለው ለ9 ወር እስር ቤት መወርወራቸውን ገልጸዋል።

አቶ ንጉሴ አይን እያየ ከመሰቃየት ሞትን መርጠው እንደነበር ገልጸው፣«በሕይወት ኖሬ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ያጠናው ጥናት ማየቴ ደስ ብሎኛል»። ጥናቱ ቢያንስ እንጂ የሚበዛ አይደለም፣ ያልተጻፉ ብዙ ግፎች አሉ። ሕዝቡ ታስሯል፣ ተገርፏል፣ ሞቷል። ግፉ እንዳይደገም አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኖ በአንድነት መቆም አለበት ብለዋል።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ «ወረራና መዋቅራዊ ዘር ማጥፋት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት» በሚል ርዕስ የተዘጋጀው የጥናት ውጤት የአጥኚ ቡድኑ ሰብሳቢ አቶ ጌታ አስራደ፤ ሕወሓት በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት የሚኖረውን የአማራ ዘር ማጥፋት ወንጀል ከመፈጸም ጎን ለጎን ሌላው የብሔሩን ተወላጅ የማጥፋት ዘመቻ አድርጎ የተጠቀመበት የታሪክና የማንነት ማጥፋት ዘመቻ ነው። ከወልቃይት ጠገዴና ጠለምት አማራ 30 በመቶ የሚሆነው የቤተሰብ አባላቱ ተገድሎበታል ብለዋል።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ያወጣው ጥናት እንዳመለከተው በወልቃይት ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ ከ1974 ዓ.ም ጀምሮ በማንነቱ የተነሳ ከፍተኛ የዘር ፍጅት ተፈጽሞበታል። በዚህም ከእያንዳንዱ ቤተሰብ 26ነጥብ5 ከመቶ ለስደት ተዳርጓል፤ 19 ነጥብ5 ከመቶ ታፍኖ የት እንደገባ አይታወቅም፤ እንዲሁም 29 ከመቶ ለሞት ተዳርጓል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመንግስት የሰላም ቁርጠኝነት ዛሬም የተጠበቀ ነው!

የኢትዮጵያ መንግስት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚገባ ተንጸባርቀዋል። ከዚያም ባለፈ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ ዋጋ እየከፈለም ቢሆን ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ደጋግሞ አሳይቷል። ይህ ስለ ሰላም ያለው የማይናወጥ አቋሙ ዛሬም የተለወጠ አይደለም። ወደ ፊትም ሊለወጥ የሚችልበት አግባብ አይኖርም።

መንግስት በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ወደ ስልጣን ከመጣበት ማግስት ጀምሮ ለመረጠው ሕዝብ የገባውን ሀገርን የማበልጸግ፤ የሕዝብን ኑሮ የመለወጥ ቃል እውን ለማድረግ ሀገራዊ ሰላም መሰረታዊ ጉዳይ እንደሆነ ያምናል። ለዚህም ለውጡ በሀገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ ባልተለመደ መልኩ በሪፎርም ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ሰርቷል።

ለውጡ በይቅርታና በመደመር ላይ መሰረት አድርጎ፤ከጠላትነት ይልቅ ወዳጅነት ላይ ከግጭት ይልቅ ሰላማዊ ሽግግር ላይ መሰረት እንዲያደርግ ረጅም ርቀት ተጉዟል። ቀደም ሲል በነበረው የፖለቲካ ስርአት ላይ ነፍጥ አንስተው ለነበሩ ኃይሎች ይቅርታ ከማድረግ ጀምሮ በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ዓላማቸውን የሚያሳኩበትን አስቻይ ሁኔታም ፈጥሯል።

ከዚህም ባለፈ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በተለይም ከኤርትራ ጋር የነበረውን ችግር በሰላማዊ መንገድ በውይይት በመፍታት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ አዲስ የሰላም አየር የሚነፍስበትን፤ የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች እርስ በርሳቸው ከመጠራጠር ወጥተው በተሻለ የወንድማማችነት መንፈስ ግንኙነታቸውን የሚያድሱበት ተጨባጭ ውጤት እንዲመዘገብም አድርጓል።

መንግስት በተቻለው አቅም ሁሉ ያለ ጥይት ድምጽ በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ሽግግሩ እውን እንዲሆን በታማኝነትና በቁርጠኝነት ሰርቷል።በዚህም በመላው ሕዝባችን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ ሀገርን እንደ ሀገር ከፍ ማድረግ ያስቻለ ክስተት ይዞ መምጣቱ ይታወሳል። የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሰላም ኖቤል ተሸላሚ መሆንም የዚሁ ሥራ አካል ነው።

የመንግስት የሰላም መሻትና ቁርጠኝነት ዋነኛ ተግዳሮት የሆነው አሸባሪው ትህነግ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ሀገርን በሽብር በመናጥ በህዝባዊ እምቢተኝነት ያጣውን ስልጣን መልሶ ለመያዝ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። ታጣቂ ኃይሎችን በማሰልጠን እና የሎጂስቲክ ድጋፍ ከመስጠት ጀምሮ ቀጥተኛ አመራር በመስጠት ሀገርን እንደ ሀገር ሰላም የሚነሱ ተግባራትን ደጋግሞ ፈጽሟል።

በጥላቻ ትርክት ሕዝብን በሕዝብ ላይ በማነሳሳት የሕዝቦችን አብሮና ተቻችሎ የመኖር የቆየ ባህል ለማደብዘዝ ሳይታክት ሰርቷል። ከዚህም አልፎ የትግራይን ህዝብ ለአስርት ዓመታት ሲጠብቅ በነበረው የመከላከያ ሰራዊት ላይ ጥቃት በመሰንዘር የሀገር ሉአላዊነት የሚዳፈር ተግባር ፈጽሟል።

ከሕዝብ ጋር እንደ ሕዝብ የምናወራርደው ሂሳብ አለኝ በሚልም በአማራና በአፋር ሕዝቦች ላይ ወረራ በማካሄድ ህዝቦቹን ሰላም በመንሳት ተዘርዝሮ የማያልቅ የጭካኔ ተግባራትን ፈጽሞባቸዋል። ሀብትና ንብረታቸውን ዘርፏል፤ አውድሟል። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩትን አፈናቅሏል፤ለጠባቂነት ዳርጓል።

እንደ ሕዝብም የትግራይ ሕዝብ በሀገሩ በሰላም የመኖር መብቱን ነፍጎ በየወቅቱ በሚያስቀምጣቸው ማስገደጃዎችና የውሸት ትርክቶች ሰላም እንዳያገኝ ከዚህ ይልቅ ለነገ ተስፋ ያደረጋቸውን ልጆቹን እየገበረ ነገዎቹ ጨለማ የቱሞሉና ተስፋ የራቃቸው እንዲሆኑ አድርጓል ፤ እያደረገም ነው።

ይህ ከፍጥረቱ ጀምሮ በሕዝቦች ሰላም እየቆመረ የፖለቲካ ትርፍ በማግኘት የሚታወቀው አሸባሪው ትህነግ በቅርቡ ለሶስተኛ ጊዜ በሀገር ላይ ጦርነት አውጆ የትግራይን ወጣት ለእልቂት እየዳረገ ይገኛል። በዚህ ጦርነት መነኩሴና አይነስውራንን ሳይቀር ከጥይት ፊት የማሰለፉ እውነታ የቡድኑን የከፋ ጨካኝነት በተጨባጭ ያሳየ ክስተት ሆኗል።

ይህ ሁሉ እየሆነበት ባለበት ሁኔታም መንግስት ስለ ሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ጠብቆ ቡድኑ በሀገርና በሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጥቃት እየተከላከለ ይገኛል።ይህ የመንግስት የመከላከል ሂደት እንደ መንግስት ካለበት የሀገርን ሉአላዊነት ከማስከበር ሕገመንግስታዊ ኃላፊነት የሚመነጭ ነው። ይህን ኃላፊነት አለመወጣት ደግሞ ሀገርን እንድትፈርስ የመፍቀድ ያህል ነው።

ይህ የሀገርን የአየርና የምድር ግዛቶች ከየትኛውም ዓይነት የውጪ ኃይል የመከላከልና የመጠበቅ ኃላፊነትን የሚያካትተው የመንግስት ኃላፊነት በየትኛውም መንገድና ሁኔታ ለድርድር የሚቀመጥ አይሆንም። ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣት ሊያማክረውም ሆነ መመሪያ ሊሰጠው የሚችል ኃይል ሆነ ቡድን ሊኖር አይችልም።

ይህ የአንድ ሀገር ህልውና /ሉአላዊነት/ የታሰረበት የመጨረሻ ገመድ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ይህን ያደርጋል ብሎ ማሰብ መንግስቱ የመጣበትን ሕዝብ ማህበራዊ መሰረት ካለመገንዘብ የሚመነጭ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የረጅም ዘመን የመንግስት ታሪክ ያለው ህዝብ ነው። ከሚመራው መንግስት የሚጠብቀውን ያውቃል፤ ለዚህ ነጋሪ የሚሻም አይደለም። ስለ ነጻነቱና ሉአላዊነቱ በየዘመኑ የከፈላቸው መስዋእትነቶችም የዚህ ተጨባጭ እውነት ማሳያ ናቸው! ስለሆነም እንደማንኛውም ጊዜ የመንግስት የሰላም እጆች ዛሬም ዝግጁ ሆነው ሀገርና ሕዝብን የመጠበቁን ኃላፊነት የሚወጣ ይሆናል!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## “ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሀል”

**ከመርደቁዮስ**

የኢትዮጵያ መንግስት በሰሜን ኢትዮጵያ ለተፈጠረው ችግር ሰላማዊ አማራጭን እየተከተለ ባለበት ወቅት፣ በመላው ህዝባችን የሰላም ጉዳይ ብዙ ተስፋ በተጣለበት ወቅት ያለጦርነት የማይኖረው አሸባሪው ሕወሓት በኢትዮጵያ ላይ ለሶስተኛ ጊዜ ጦርነት ከፍቷል፡፡ ሀገሪቱም ወደ ጦርነቱ ተገዳ ገብታለች፡፡ ሆኖም ጦርነቱን እየመከተች፣ ለሰላማዊ አማራጩ ተስፋ ሳትቆርጥ አሁንም እጇን ለሰላም ዘርግታለች፡፡

በርግጥ ቡድኑ ቀደም ባሉት ጊዜያት ጦርነቱን ሊጀምረው እንደሚችል ምልክቶች አስቀደሞ ታይተዋል፡፡ የተኩስ አቁም ተጣሰ፣ የሰላም ንግግሩ ቅድመ ሁኔታዎች አልተፈጸሙም፣ ወዘተ. ሲል መቆየቱ ፤ ይህን ተከትሎም የሰላም ንግግሩ ቴክኒካሊ ፈርሷል ማለቱ “የዘፈን ዳር ዳሩ “እንዲሉ ነበር።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ቡድኑ ባጋጠሙት አስገዳጅ ውስጣሳዊና ውጪያዊ ችግሮች ጦርነቱን ለመጀመር ተገዷል። በዚህም ከትናንት ስህተቶች መማር ሳይችል ቀርቶ የትግራይ ወጣቶችን ለዳግም እልቂት እየዳረገ ይገኛል።

ጦርነት የባህል ጨዋታዬ ነው የሚለው ይህ ቡድን፤ የጀመረውን ጦርነት ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት አስቦ ከጦርነት ከመቆጠብ ይልቅ፤ ጦርነት ከፍቶ ጦርነቱን መንግስት ነው የጀመረው በሚል አደንቋሪ ጩኸቱ አለም አቀፉን ማህበረሰብ ለማሳሳት እየሞከረ ይገኛል። ቡድኑ ጦርነት ከፍቶ ተከፈተብኝ ሲል ይህ የመጀመሪያው አይደለም፤ ሰሜን እዝ ላይ ራሱ ክህደትና ጥቃት ፈጽሞ፣ ጦርነቱን የጀመረው መንግስት ነው ለማለት ድፍረት የነበረው ነው፤ አሁንም የሆነው ተመሳሳይ ነገር ነው፡፡

መንግስት ስለ ሰላም ጦሩን ከትግራይ ክልል ባወጣ ማግስት በተያዘበት የጦርነት አባዜ ምክንያት “ ከአማራ ክልል ጋር የማወራርደው ሂሳብ አለኝ “ ብሎ በአማራ እና በአፋር ክልሎች ላይ ወረራውን በማካሄድ ወደመሀል ሀገር ዘልቆ በህዝባዊ እንቢተኝነት ያጣውን ስልጣን መልሶ ለማግኘት ሞክሯል፡፡

በዚህ ሶስተኛው የጦርነት ድግሱም እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው፡፡ ለጦርነቱ በቂ ዝግጅት ማድረጉን ቡድኑ በተለያዩ ጊዜያት በሰጣቸው መግለጫዎች ሲያስታውቅ ቆይቷዋል፤ በሀገሪቱ የሰላም አማራጭ እየተቀነቀነ

> **ቡድኑ ጦርነት ከፍቶ ተከፈተብኝ ሲል ይህ የመጀመሪያው አይደለም፤ ሰሜን እዝ ላይ ራሱ ክህደትና ጥቃት ፈጽሞ፣ ጦርነቱን የጀመረው መንግስት ነው ለማለት ድፍረት የነበረው ነው፤ አሁንም የሆነው ተመሳሳይ ነገር ነው፡፡**
>
> **መንግስት ስለ ሰላም ጦሩን ከትግራይ ክልል ባወጣ ማግስት በተያዘበት የጦርነት አባዜ ምክንያት — ከአማራ ክልል ጋር የማወራርደው ሂሳብ አለኝ — ብሎ በአማራ እና በአፋር ክልሎች ላይ ወረራውን በማካሄድ ወደመሀል ሀገር ዘልቆ በህዝባዊ እንቢተኝነት ያጣውን ስልጣን መልሶ ለማግኘት ሞክሯል፡፡**
>
> **በዚህ ሶስተኛው የጦርነት ድግሱም እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው፡፡**

ባለበት ሁኔታ አሸባሪው በአማራና በአፋር አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ የተለያዩ ትንኮሳችንም ያደርስ ነበር።

በአፍሪካ ህብረት በኩል ለሚደረገው የሰላም ንግግር ራሱን ዝግጁ ከማድረግ ይልቅ ቅድመ ሁኔታዎችን ሲደረድርም ቆይቷል፤ ነገሮች እሱ በሚፈልገው መልኩ ሳይሄዱ መቅረታቸውን ሲገነዘብ ደግሞ የሰላም ንግግሩ ጉዳይ ቴክኒካሊ ፈርሷል ወደ ማለት ተሸጋግሮ ነበር፡፡ የዚህ ሁሉ ዳርዳርታ ምን ለማድረግ እንደሆነ የማይገነዘበው ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ከዚህም በላይ ታጣቂዎቹ በሚገባ የሰለጠኑ መሆኑንም በየአደባባዩ ሲያውጅ ነበር ፡፡ ልክ እንዳለፈው ጦርነት ሁሉ ከትህነግ ታጣቂዎች ፊት የሚገባ ቁጥር ስፍር የሌለው ህጻናት፣ እናቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ወዘተ. የተካተቱበት ጀሌዎችን እንደ ሰብአዊ ጋሻ አድርጎ ሲመለምል ነበር፡፡

ለትግራይ ህዝብ የገባ የእርዳታ አቅርቦቶችን ከህዝብ ጉሮሮ በመንጠቅ ለተዋጊ ሀይሉ ራሽን እንዲሆን በየመጋዘኑ አከማችቶ የጦርነት መጀመሪያ ጊዜውን ሲጠባበቅ የነበረ ሲሆን፤ ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ከአለም የምግብ ድርጅት መጋዘን ላይ የፈጸመው የነዳጅ ዘረፋም የዚሁ የጦርነት ዝግጅቱ አንድ ምእራፍ ነበር።

ቡድኑ በአንድ በኩል በትግራይ ህዝብ የሚነሱ ልጆቻችን የታሉ ጥያቄን መመለስ አለመቻሉ፤ በሌላ በኩል ለቡድኑ እኩይ ተግባር የፋይናንስና የፕሮፓጋንዳ ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት በቡድኑ ያላቸውን እምነት እያጡ መሄዳቸው የፈጠሩት ጫና ጦርነቱን እንዲጀምር አስገድደውታል።

ጦርነቱን መጀመሩ እየጋለቡት ለሚገኙት ታሪካዊ ጠላቶቻችን እንዳልሞተ ፤ በህይወት መኖሩን ለማሳወቅ እንደ አንድ አማራጭ የወሰደው ነው ፤ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችም ከቁዘማቸው ወጥተው በአዲስ የአይዞህ ባይነት መንፈስ እንዲነሳሱና መኖሩን አምነው ድጋፋቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግ ጭምር ነው ።

ይህ በትግራይ ህዝብ መከራና በትግራይ ወጣቶች ደም የሚቆመር የፖለቲካ ቁማር የአሸባሪውን ሕወሓት እድሜ ከማርዘም ያለፈ ፋዳ የሚኖረው ባለመሆኑ የትግራይ ህዝብ እውነታውን በስክነት ሊመለከተው ይገባል።

“ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሀል” እንደሚባለውም የትግራይ ህዝብን ጨምሮ አለም አቀፉ ህብረተሰብ ያለጦርነት መኖር የማይችለው ይህ ቡድን መንግስት ጦርነት ከፈተብኝ ለሚለው የማደናገሪያ ጩሀት ጆሮውን ሊሰጥ አይገባም።

ቀድሞውንም ቢሆን ስለሰላም ሲያዜምና ለሰላም ብዙ እድሎችን ሲሰጥ የቆየው ፤ ከዛም ባለፈ የቡድኑን ትንኮሳዎች ስለሰላም በልበ ሰፊነት ሲያልፍ የነበረው ፤ከሁሉም በላይ ሰላም እንደ ሀገር ለጀመርነው ልማት ስሌት ወሳኝ አቅም ነው ብሎ የሚያምነው መንግስት ወደ ጦርነት ለመግባት ምን ምክንያት ይኖረዋል ?

የአለም ምግብ ፕሮግራምን እርዳታ ጭነው ወደ ትግራይ የሚገቡ ከባድ መኪኖችን ለወታደራዊ አገልግሎት እስከማዋል የደረሰ ዘረፋ የፈጸመ ቡድን ነው፡፡ ይህን ድርጊት አምና ፈጽሞታል፤ ዘንድሮም ጭነት ይዘው ከገቡ ከባድ መኪኖች ብዙ ያልተመለሱ አሉ፤ ለምን አልተመለሱም ለሚለው ደግሞ ባለፈው አመት ያልተመለሱበትን ምክንያት መጥቀስ የሚያስኬድ ይሆናል፡፡

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ



በግፍ በ550 ሺ ብር ሲሸጥ የነበረው ይሄ ቤት 11 ነጥብ ሰባት ሚሊየን ብር አውጥቷል፤

# በኢፕድ ዘገባ - የታበሰ እንባ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ‹‹ፍረዱኝ›› በሚል አምደ ስር የተለያዩ የምርመራ ዘገባዎችን ሲሰራ ቆይቷል። አሁንም እየሰራ ይገኛል። በሚሰሩት የዘገባ ሥራዎች የበርካታዎችን እንባ ማበስ ተችሏል። ቀደም ሲል በአምዱ ተስተናግደው በምርመራ ዘገባ ጉዳያቸው ቀርቦ ጋዜጣው ላይ ለንባብ ከበቁ በኋላ ውጤት የተገኘባቸውን በተለያዩ ጊዜያት አቅርበናል። ዛሬ ደግሞ ሰኔ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ለንባብ በቅቶ ውጤት የተገኘበት እና ተበዳዮችም ቀርበው በአካል በድምፅም እና በደብዳቤ ድርጅቱን በተለይም የዝግጅት ክፍሉን ያመሰገኑበትን ስራ ያለፈውን በማስታወስ የተገኘውን ውጤት እንደሚከተለው ለንባብ አቅርበናል።

«በመጦሪያ እድሜዬ ልጆቼ ጎዳና ሊጥሉኝ ነው» በሚል ርዕስ በአንድ ቤተሰብ መካከል የተፈጠረን አለመግባባት የተመለከተ የምርመራ ዘገባ ሰርተን ነበር። በዚህ የምርመራ ዘገባ ወደ ዝግጅት ክፍሉ የመጡት አቤቱታ አቅራቢዎች የ86 ዓመት አዛውንት እማሆይ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ እና ልጃቸው ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ ነበሩ።

**ፍሬ ነገሩ**

የእማሆይ አለምነሽ ልጅ እና የወይዘሮ መድሃኒት እህት በሆነችዋ ወይዘሮ በቀለች ሃይሌ እና በልጆቿ (በእማሆይ አለምነሽ የልጅ ልጆቻቸው) ከኖሩበት ቤት ሊያስወጧቸው እንደሆነ በመጥቀስ አቤቱታቸውን ሕዝብና መንግስት አይቶ ይፍረደኝ ሲሉ ቀርበው በደላቸውን አሰምተው ነበር። እማሆይ አለምነሽ ልጆቻቸውን እና የልጅ ልጆቻቸውን ያሳደጉበት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ ስድስት የቤት ቁጥሩ 834 የሚገኘውን ቤት ፍትህን ባልተከተለ አኳኋን ሊያባርሯቸው መሆኑን ነበር የተናገሩት።

በዚህ ቤት አምስት ልጆችን እና በርካታ የልጅ ልጆችን በማሳደግ ለወግ ለማዕረግ እንዳበቁበት አዛውንቷ ይናገራሉ። ይሁን እንጂ በአሁን ወቅት በእርጅና ዘመናቸው እጦርበታለሁ፤ ብለው ተስፋ ካደረጉትና ጠብቀው ካኖሩት ቤት ሊነጠቁ መሆኑን ነው የተናገሩት። ሰኔ 1 ቀን2014 ለንባብ አብቅቶታል።

**ውዝግብ የፈጠረው ቤት የኋላ ታሪክ**

እማሆይ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ ከሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ ጋር በትዳር ይተሳሰራሉ። ጥንዶቹ በትዳር ዘመናቸው በቀለች ሃይሌ ፤መድሃኒት ሃይሌ ፤ ፍቃዱ ሃይሌ ፤አየለች ሃይሌ እና ሰለሞን ሃይሌ የተባሉ አምስት ልጆችን ወልደዋል። ሻለቃ ባሻ ሃይሌ ወታደር በመሆናቸው ከባለቤታቸው ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ እና ከአምስት ልወጆቻቸው ጋር በካምፕ ውስጥ መኖር የውዴታ ግዴታቸው ነበር።

ከአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ እስከ ደርግ ዘመነ መንግስት የመጀመሪያ አምስት አመታት ድረስ ሻለቃ ባሻ ሃይሌ በውትድርና አገልግለዋል። በንጉሱ ዘመን በሰሩት ወታደራዊ ጀብዱም በአዲስ አበባ ከተማ የመኖሪያ ቤት እንዲሰጣቸው በመንግስት ተወስኖላቸዋል። አሁን ጎፋ መብራት ሃይል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ባዶ ቦታ ተሰጣቸው።

የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ ቤት ሰርተው ቤተሰባቸውን በራሳቸው ቤት ለመኖር ከነበራቸው ጉጉት የተነሳ ያልለማውን ጫካ መንጥረው አካባቢው ለቤት መስሪያ የተመቸ እንዲሆን አድርገው አዘጋጁት። ነገር ግን በስንት ውጣ ውረድ ጫካ መንጥረው ያለሙትን ቦታ ለመብራት ሀይል ልማት ሊውል በመታሰቡ ቦታውን ለመንግስት እንዲለቁ ተገደዱ። በምትኩ ጎፋ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ቀደም ብሎ ሌተናል ኮሎኔል በቀለ ባልቻ በተባሉ የጦር መኮንን በርስትነት ሲተዳደር የነበረው ቦታ ይሰጠኝ ሲሉ በ1966 ዓ.ም ለጽህፈት ሚኒስቴር ያመለክታሉ።

ጉዳዩም በጽህፈት ሚኒስቴር ተቀባይነት አግኝቶ በሰኔ ወር 1966 ዓ.ም በቁጥር 3661/8/116/01 ለአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቦታ እንዲሰጣቸው ማዘዣ ደብዳቤ ተላከ። የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃም 116/3ዕ/67 በቀን 7/2/1967 ዓ.ም ለርስት እና መሬት ቅየሳ ዋና ክፍል ደብዳቤ ተጻፈ። በደብዳቤውም ሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ የጠየቁት ጥያቄ ተቀባይነት ስላገኘ እንዲፈጸምላቸው ታዘዘ። በዚህም መሰረት ኮሎኔሉ በይዞታነት ሲያስተዳድሩት የነበረው አምስት መቶ ካሬ ሜትር ለሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ በ1967 ዓ.ም ተሰጠ።

የአምስት ልጆች አባት ሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ፣ በ1971 ዓ.ም ለግዳጅ በምስራቅ ኢትዮጵያ ግዛት ስር በምትገኘው ገዋኔ አካባቢ ለግዳጅ ተላኩ። በዚሁ ዓመት ሻለቃ ባሻ ሀይሌ በግዳጅ ላይ እያሉ ባለቤታቸውን እና አምስት ልጆቻቸውን ጥለው ከዚህች ምድር ተሰናበቱ። የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቤተሰቦች የካምፕ ህይወትም በዚሁ አመት አበቃ። ወይዘሮ አለምነሽ እና ልጆቻቸው የካምፕ ህይወትን በመተው ዛሬ ላይ ውዝግብ በተነሳበት ቦታ አመሩ። ይህን ተከትሎ የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሊ ባለቤት ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ የልጆቻቸው ሞግዚት መሆናቸውን በ1972 ዓ.ም በህግ አሳወጁ።

ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ እና ልጆቻቸው ህይወትን ያለሻለቃ ባሻ ሃይሌ ሊያስቀጥሉ ግድ ሆነ። በወቅቱ ለሀገራቸው ሲሉ መስዋዕት የሆኑ የወታደር ልጆች በውጭ ሀገር በመሄድ እንዲማሩ መንግስት እድሉን አመቻቸላቸው። የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ልጆች ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ እና አቶ በፍቃዱ ሃይሌ በ1972 ዓ.ም ለትምህርት ወደ ሀገረ ኩባ ተላኩ። ወደ ሀገረ ኩባ የተላኩት የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ልጆች አቶ በፍቃዱ ሃይሌ እና ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ በቤተሰብ ናፍቆት ሳቢያ በተፈጠረ መጨናነቅ ለከፍተኛ ድብርት እና ህመም ተዳረጉ።

አቶ በፍቃዱ ሃይሌ በ1977 ዓ.ም ወደ እናት ሀገራቸው ሲመለሱ ፤ ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ ደግሞ ወንድማቸውን ተከትለው 1978 ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። ሁለት ልጆቻቸውን ወደ ሀገረ ኩባ የላኩት እናት ወይዘሮ በቀለች ሃይሌ፣ ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ ሲያሳድጉ ቆዩ። በቤተሰቡ ውስጥ የነበረው ፍቅር ለሰፈር የሚያስቀና ነበር።

ወደ ኩባ የሄዱት ልጆች ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ያረፉት እና ኑሯቸውን የቀጠሉት በእናታቸው እና በአባታቸው ቤት ነበር። ቀንን ቀን ሲወልደው ወይዘሮ በቀለች ሃይሌ የቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ እናታቸውን ወይዘሮ አለምነሽን በምስጢር ቤቱን እንዲያወርሷቸው ይጠይቃሉ። ወይዘሮ አለምነሽም ለማንም ጉዳዩን ሳያሳውቁ እና ሳይሰሙ በ1985 ዓ.ም ቤቱን ለወይዘሮ በቀለች ብቻ ያወርሳሉ። ነገሩን በምስጢር ማድረጋቸው እየቆየ የከነከናቸው እናት ለልጃቸው ያወረሱትን ቤት ከልጃቸው መውሰድ ፈለጉ።

**ባለማወቅ ያወረሱትን ቤት የማስመለስ ጥረት**

ውርሱን የፈቀዱት እናት በስህተት ማውረሳቸውን ጠቅሰው ቤቱን እንድትመልስላቸውም ልጃቸውን ይጠይቃሉ። ልጅም ‹‹ቤቱ የእኔ እንጂ ያንቺ ስላልሆነ ቤቱን እንድመልስልሽ የመጠየቅ መብት የለሽም›› ይላሉ። ይህን ተከትሎ አራቱ ልጆች ስለጉዳዩ ሳያውቁ እና ሳይሰሙ እናት ወይዘሮ አለምነሽ በ2000 ዓ.ም ‹‹በውርስ የሰጠኋትን ቤት ትመልስልኝ›› ሲሉ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወሰዱት።

ጉዳዩ በፍርድ ቤት ሲታይ ቆይቶ እናት በፍርድ ቤት ክርክር ይረታሉ። እናትን የፍርድ ባለዕዳ እንዲሆኑ ያደረጋቸውም ቤቱን ለልጃቸው ካወረሱት በርካታ አመታት በመቆጠሩ የይርጋ ጊዜ ገደብ አልፎበታል በሚል ነበር። በ2006 ዓ.ም የሻለቃ ባሻ ቡሊ አራቱም ልጆች ስለጉዳዩ ይሰማሉ። የሰሙትን ማመን የከበዳቸው የሻለቃ ባሻ ልጆች ‹‹እንዴት እንደዚህ ይሆናል?›› ሲሉ እናታቸውን እና እህታቸውን ይጠይቃሉ። እናት ሳያውቁ ተታልለው ለወይዘሮ በቀለች እንዳወረሱ እና ጉዳዩን በደንብ ከተረዱ

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ፍረዱኝ

በኋላ ግን በስጦታ ያወረሱትን ቤት ለማስመለስ እስከ ፍርድ ቤት መሄዳቸውን ለልጆቻቸው ያስረዳሉ። በብቸኝነት ቤቱን የወረሰችው ልጅ ደግሞ ቤቱ የእርሷ እንደሆነ እና ስለቤቱ ማንም እንደማያገባው አስረግጣ ለወንድሞቿና ለእህቶቿ ነገረቻቸው። ይህን ተከትሎ በፍቅር እና በመተሳሰብ የነበረው ቤተሰብ በመካከሉ ነፋስ ገባ። ቤተሰተቡ በከፍተኛ ደረጃ መግባባት ከበደው።

ይህ በእንዲህ እያለ እናት ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኝ በ1971 ዓ.ም ባለቤታቸው በግዳጅ ላይ መሰዋታቸውን ተከትሎ በ1972 ዓ.ም ቤተሰቡን ለማሳድግ የሞግዚነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከህጋዊ አካል ተቀብለው ነበር። ይሁንና አሁን በቤቱ ላይ ህጋዊ ወራሽነታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመኖሩ ቤቱን ከባለቤታቸው በውርስ ስለማግኘታቸው የሚያረጋግጥ የባለመብትነት የምስክር ወረቀት ይሰጠኝ ሲሉ በድጋሚ በ2006 ዓ.ም ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አመለከቱ።

ክፍለ ከተማውም ህጋዊ ወራሽ ስለመሆናቸው ቤቱንም በውርስ ከሻለቃ ባሻ ሃይሌ እንደወረሱት የሚገለጽ ምስክር ወረቀት በ2006 ዓ.ም ይሰጣቸዋል። ይህ በእንዲህ እያለ ቤቱ የአባታችን ስለሆነ ለእኛም ይገባናል ሲሉ የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ልጅ የሆኑት ወይዘሮ መድሃኒት፣ አቶ ሰለሞን፣ ወይዘሮ አየለች እና አቶ በፍቃዱ ለፍርድ ቤት አቤት አሉ። በፍርድ ቤት የነበረው ክርክር እና ውሳኔ ከባለውርስ ባለመብትነት ጋር ተያይዞ በፍርድ ቤት የነበረው ክርክር ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ሰበር የደረሰ ሲሆን፣ ከስምንት አመት በላይ ፈጀ።

በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው የፍርድ ቤት ክርክር ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ፣ አቶ ፍቃዱ ሃይሌ፣ ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ ከሳሽ፤ እናት ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ እና ወራሽ እህት በቀለች ሃይሌ በቅደም ተከተል አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል። በፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ከሳሽ ቤቱ የአባታችን ስለሆነ እና እኛም አንደኛ ደረጃ ህጋዊ ወራሽ ስለሆንን ከቤት ውርስ ጋር ተያይዞ የሚከናወኑ ማናቸውም አይነት መብቶች እኛንም ይመለከተናል አሉ።

እናትም የመጀመሪያ ልጄ ወይዘሮ በቀለች «እኔ ያልተማርኩ በመሆኔ እኔን በማታለል ቤቱን ከቤተሰቡ ደብቃ የወረሰችው በመሆኑም ቀሪ ልጆቼም በቤቱ የሚኖራቸው መብት ይከበርላቸው» ሲሉ ከሳሽ ልጆቻቸውን ደግፈው ቆሙ። ሁለተኛ ተከሳሽ ወይዘሮ በቀለች በበኩላቸው፤ «አራቱም ልጆች በወራሽነት ያልተመዘገቡ እና ከጅምሩ ቤቱ የእኔ እንጂ የእናታችንም ሆነ የአባታችን የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቤት ስላልሆነ ከሳሽ ወንድም እና እህቶቼ ከውርስ ጋር ተያይዞ ያነሱት የይገባኛል ጥያቄ አግባብነት የለውም» ሲሉ ተከራከሩ።

ቤቱን የወረሱት ወይዘሮ በቀለች ከመጀመሪያም ጀምሮ ቤቱ የእኔ እንጂ በውርስ የተገኘ አይደለም ማለታቸውን ተከትሎ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት ቤቱ የማን ነው? የሚለውን ለማጣራት ጉዳዩን ለውርስ አጣሪ መራው። ይህን ተከትሎ የውርስ አጣሪው አካል ቤቱ በ1967 ዓ.ም ለሻለቃ ባሻ እንደተሰጣቸው እና በ1971 ዓ.ም ሻለቃ ባሻ በግዳጅ ላይ እያሉ በማረፋቸው በ1972 ዓ.ም እናት ወይዘሮ አለምነሽ ደግሞ ቤቱን የልጆች ሞግዚት ሆነው እንዳስተዳደሩት አረጋገጠ። እንዲሁም በ1985 ዓ.ም ወይዘሮ አለምነሽ ለተከሳሽ ወይዘሮ በቀለች በስጦታ ውል ማስተላለፋቸው ታውቆ፤ ይሁን እንጂ በፍታብሄር ህግ ቁጥር 1195(1) መሰረት ከቤቱ ጋር ተያይዞ የምስክር ወረቀት ያገኘ ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሆኖ እንደሚቆጠርለት ስለሚደነግግ ቤቱን በስጦታ ውል እናት ስላስተላለፉት እና ቤቱን በተመለከተ ወይዘሮ በቀለች የምስክር ወረቀት በህግ ከተፈቀደለት አካል ስለተሰጣቸው ከ1985 ዓ.ም ጊዜ ጀምሮ ወይዘሮ በቀለች የሚያስተዳድሩት የግል ንብረት እንጂ የውርስ ንብረት አይደለም ሲል መለሰ።

ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ ባደረገው ተጨማሪ ምርመራ የውርስ አጣሪው የደረሰበት ውሳኔ ትክክል አይደለም በሚል ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። ይህ የፍርድ ቤት ውሳኔ ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የጸና ሆነ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሁሉም ልጆች የወራሽነት ማረጋገጫ ከፍርድ ቤት እንዲያመጡ ተጠየቀ። አራቱም ከሳሽ ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች መሆናቸው ተረጋገጠ። ይሁን እንጂ ከሻለቃ ባሻ ሞት በኋላ ወደ ኩባ ያልሄዱት ልጆች የወራሽነታቸው መብታቸው በይርጋ ታገደ። የይገባኛል ክርክሩም ኩባ በሄዱት ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ ከሳሽ እናት ወይዘሮ አለምነሽ እና ወራሽ ልጃቸው ወይዘሮ በቀለች ተከሳሽ ሆነው ቀረቡ።

ክርክሩም እስከሰበር ሰሚ ችሎት ዘለቀ። በክርክሩም «ቤቱን በስጦታ ያወረስኩት ያልተማርኩ ስለሆነ በማታለል እና በማጭበርበር ነው» ሲሉ እናት ለሁሉም ለፍርድ ቤቶች አስረዱ። ይሁን እንጂ የቤቱን ግማሽ ወይዘሮ በቀለች በስጦታ መውረሳቸውን እና አሁን ላይ ደግሞ የእናት ቤቱን የማስመለስ ህጋዊ መብት በይርጋ የተገደበ መሆኑን አስገንዘቦ በውርስ ለወይዘሮ በቀለች የተሰጠው ግማሽ ቦታ ለወይዘሮ በቀለች እንዲሰጥ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ወሰነ። ግማሹ የሻለቃ ባሻ ሃይሌ ድርሻ ደግሞ ለሶስት ማለትም ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ ፣ አቶ ሰለሞን ሃይሌ እና ለወይዘሮ በቀለች እንዲከፋፈሉ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሳኔ ሰጠ።

በዚህ ውሳኔ መሰረት የቤቱ ግማሽ እናት ለወይዘሮ በቀለች በስጦታ ውል ያወረሱት ስለሆነ በወይዘሮ በቀለች ወራሽነት እንዲጸና እና ግማሹ የአባት ድርሻ ደግሞ ለሶስት እንዲካፈሉት ተወሰነ። ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌ ፣ አቶ ፍቃዱ ሃይሌ ፣ ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ «ቦታውን እናታችን ከአባታችን ያገኘችው እንጂ በራሷ ያፈራችው ስላልሆነ ለአንድ ልጇ ብቻ የማውረስ መብት የላትም። ቤቱ የአባታችን ስለሆነ እና አባታችን ሲሞት አሁን ለክርክር የቀረቡት ልጆች ለአቅመ አዳም እና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ስለነበር እናት ልጆችን በሞግዚትነት ለማስተዳደር ቤቱን በሃላፊነት ተሰጣት እንጂ አልወረሰችም። ስለሆነም የራሷ ያልሆነ ንብረት ማውረስ አትችልም።» ሲሉ ተከራከሩ።

በመጨረሻም ክርክሩን ሲያዳምጥ የነበረው ፍርድ ቤት የአከራካሪው ቤት ግማሽ የሚሆነው እናት ለወይዘሮ በቀለች ያወረሱት ስለሆነ ለወይዘሮ በቀለች የተሰጠው ቦታ ባለበት እንዲጸና እና ግማሹ የአባታቸው ድርሻ ደግሞ ከእናታቸው ውርስ ያገኙትን ወይዘሮ በቀለችን ጨምሮ ለሶስት እንዲከፋፈሉ ተወሰነ።

## የአቤቱታ አቅራቢዎቹ ጥያቄ

የፍርድ ባለእዳን ወይዘሮ መድሃኒት ሃይሌን እና እናታቸውን እማሆይ አለምነሽ አቤት እንዲሉ ያስገደዳቸው አብይ ምክንያት ከውርስ የተገለሉት ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ በእናት እና በአባት አንድ በመሆናቸው አንደኛ ደረጃ ህጋዊ ወራሾች መሆናቸው እየታወቀ ኩባ ሀገር ስላልሄዱ ብቻ ከአባታቸው ድርሻ የወራሽነታቸው መብታቸው በይርጋ መታገዱ ትክክል አይደለም። ለምን ይህ ሆነ የሚል ነበር።

ወይዘሮ አየለች ሃይሌ እና አቶ ሰለሞን ሃይሌ ከአባታቸው የወራሽነት ባለመብትነታቸው ከወይዘሮ በቀለች ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ሳለ በይርጋ መታገድ ካለበት የወይዘሮ በቀለችም በይርጋ መታገድ ሲገባው ከላይ የተጠቀሱት የቤተሰቡ አባል የወራሽነት መብት ነፍጎ ለወይዘሮ በቀለች ብቻ በይርጋ የማይታገድ መብት መሠጠቱ ፍትሃዊ አይደለም የሚል ነበር።

ሌላው ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ ባለቤታቸው ሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቡሌ እንደሞቱ በአሙቱ በህግ የተፈቀደላቸው ለአቅመ አዳም እና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ልጆችን በሞግዚትነት እንዲንከባከቡ እንጂ ከሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቤቱን እንዲወርሱ አይደለም። ወራሽ ስለመሆናቸው የሚያሳይ ሰነድ የለም። ከሻለቃ ባሻ ሃይሌ ቤቱን በህጋዊ መንገድ መውረሳቸው የሚመለከተው አካል አረጋግጦ ምስክር የሰጣቸው በ2006 ዓ.ም ነው። ይሁን እንጂ ይህ ህጋዊ የውርስ ሰነድ በሌለበት እናት ወይዘሮ አለምነሽ ወንድምአገኘሁ በ1985 ዓ.ም ለልጃቸው ለወይዘሮ በቀለች ሃይሌ አውርሰዋል። ይህ ደግሞ በግልጽ የሚታይ የህግ ክፍተት ያለበት ሆኖ ሳለ ፍርድ ቤቱ ወይዘሮ በቀለች ከእናታችን በስጦታ ያገኙትን ውርስ በይርጋ ለወይዘሮ በቀለች ማገዱ አግባብነት የለውም። ሲሉ አቤት ብለዋል።

በሶስተኛ ደረጃ አቤት እንዲሉ ያስገደዳቸው እና በዋናነት ትኩረት እንዲሰጠው የፈለጉት ደግሞ ከፍርድ ቤት ውሳኔ በኋላ የተተገበረው የፍርድ አፈጻጸም አካሄድ ጉዳይ ነበር። የቦታው ግማሽ ለሶስት እንዲካፈል ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ቢሰጥም ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ በዓይነት ከማካፈል ይልቅ ለቤቱ ጨረታ በማውጣት እንዲካፈሉ እየጣረ ነው የሚል ነበር። ይህ ደግሞ እማሆይ አለምነሽን በዚህ እድሜያቸው ጎዳና ላይ የሚጥል ነው የሚል ነበር።

የፍርድ አፈጻጸም ቢሮ ላይ የቀረበ አቤቱታ

«ቦታው በጨረታ ይሸጥ ቢባል እንኳን የፍርድ አፈጻጸም ለጨረታ ያወጣው የቦታው ልኬት ትክክል አይደለም። ቦታው በካርታ 500 ካሬ ሜትር ይሁን እንጂ የክፍለ ከተማው የመሬት አስተዳደር ባደረገው የማጣሪያ ልኬት መሰረት የቦታው ስፋት 680 ካሬ ሜትር ነው። ይሁን እንጂ ህግ አፈጻጸም ቦታው 500 ካሬ ሜትር ብቻ እንደሆነ በማስመሰል ቦታውን በአይነት ከማካፈል ይልቅ በሃራጅ እንዲሸጥ ጨረታ አውጥቶበታል። ይህ የፍርድ አፈጻጸም ቢሮ አካሄድ ትክክል ስላልሆነ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ» ሲሉ ለፍርድ ቤት እንደገና አቤት ማለታቸውን ወይዘሮ መድሃኒት ይናገራሉ።

ፍርድ ቤትም ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ ፃፈ። የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮም የፍርድ ቤት ትዛዝን ተቀብሎ እንደገና ጨረታ አወጣ። ይሁን እንጂ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ አጠቃላይ የቦታው ስፋት 680 ካሬ ሜትር ሆኖ ሳለ የተስተካከለ ከክፍለ ከተማ የተሰጠን የቦታ ልኬት 580 ካሬ ሜትር ነው በማለት የቦታው ግማሽ 290 ካሬ ሜትር ለወይዘሮ በቀለች በመስጠት፤ ግማሹን 290 ካሬ ሜትር ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ በማውጣት ሊሸጠው ነው። የሚል አቤቱታ አቀረቡ።

## የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ ምላሽ

በፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ ጉዳዩን በበላይነት ሲከታተሉ የቆዩት በፍርድ የቴክኒክ ክፍል ባለሙያ አቶ እስማኤል ኢብራሂም፤ በቢሮው በፍርድ ቤት የሚወሰኑ ውሳኔዎችን በክፍለ ከተማ ከሚገኙ መረጃዎች ጋር በማመሳከር የፍርድ አፈጻጸም ስራዎች ይከናወናሉ። ማለታቸውን ተከትሎ የእነወይዘሮ መድሃኒት አቤቱታን በመግለፅ ፍርድ ቤቱ በአይነት ይካፈሉ ከተባለ ለምን በዓይነት ለማካፈል አልተቻለም? ሲል የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ይጠይቃል።

የቴክኒክ ክፍል ባለሙያው አቶ እስማኤል በሰጡት ምላሽ፤ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮ የመጀመሪያ ምርጫው የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን በዓይነት ማካፈል ነው። ነገር ግን በአዲስ አበባ መሬት አስተዳደር መመሪያ መሰረት አንድ ቦታ ራሱን ችሎ ሊለማ የሚችለው 150 ካሬ ሜትር እና ከዚያ በላይ ስፋት ሲኖር ብቻ ነው። እነወይዘሮ መድሃኒት ለሶስት ይካፈሉት የተባለው ቦታ 290 ካሬ ሜትር ነው። ይህ ደግሞ ለሶስት ሲካፈል በአዲስ አባበ ከተማ አስተዳደር መመሪያ መሰረት ራሱን ችሎ መልማት ስለማይችል በዓይነት ለማካፈል አይቻለም። ይህ አልሆን ሲል በስምምነት ቦታው ተሸጦ እንዲካፈሉት ይደረጋል። ይህ አልሆን ሲል ደግሞ በሃራጅ ጨረታ ይወጣበት እና ቦታው ተሸጦ ፍርድ ቤት በወሰነው መሰረት ለእያንዳንዳቸው የድርሻቸው እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

የእነ ወይዘሮ መድሃኒትም በአንደኛው እና በሁለተኛው አማራጭ የፍርድ አፈጻጸሙን ማስኬድ ባለመቻሉ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቢሮው ሶስተኛውን አማራጭ ለመምረጥ ተገዷል። የፍርድ ባለእዳዋ ወይዘሮ መድሃኒት ቤቱ መሬት ላይ ያለው ልኬት 680 ካሬ ሜትር ሆኖ ሳለ በካርታ ላይ ያለውን 500 ካሬ ሜትር ነው በማለት 250 ካሬ ሜትር ብቻ እንድንወስድ እየተደረገ ነው። በዚህ ደግሞ ለጨረታ የቀረበው ቦታ ርካሽ እንዲሆን ያደርግብናል ሲሉ መጠየቃቸውን በመጠቀም እዚህ ላይም ምላሽ እንዲሰጥበት የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ቢሮውን ጠይቋል።

አቶ እስማኤል በሰጡት ምላሽ፤ «እውነት ነው ለመጀመሪያ ጊዜ በፍርድ አፈጻጸም ጨረታ የወጣበት በ500 ካሬ ሜትር ስፋት ብቻ ነበር። ነገር ግን የፍርድ በለእዳዋ ከክፍለ ከተማ አስጽፈው ባመጡት ደብዳቤ ቦታው 580 ካሬ ሜትር እንደሚሆን ስለተረጋገጠ የመጀመሪያው 250 ካሬ ሜትር ላይ የወጣው ጨረታ ተሰርዞ፤ ለሁለተኛ ጊዜ ተስተካከልሎ 290 ካሬ ሜትር በሚል በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጨረታ ወጥቷል።

ይህን ተከትሎ የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል የፍርድ ባለዳዋ የሚሉት ቦታው 680 ካሬ ሜትር ይለካል ነው። እዚህ ላይ የእናንተ ምላሽ ምንድን ነው? በሚል ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን የፍርድ አፈጻጸም ስራ የሚከናውነው ከክፍለ ከተማ የመሬት አስተዳደር በሚገኝ መረጃዎች መሰረት ነው ሲሉ አቶ እስማኤል ምላሽ ሰጥተዋል። አክለውም የክፍለ ከተማው የመሬት አስተዳደር ደግሞ የላከው ደብዳቤ ቦታው በካርታ 500 ካሬ ሜትር እንደሆነ እና በመሬት ላይ ልኬቱ ደግሞ 580 ካሬ ሜትር መሆኑን የሚሳይ ነው። ስለዚህ ክፍለ ከተማው ከላከው መረጃ ውጭ ሊካፈል አይችልም ሲሉ ተናግረዋል። ክፍለ ከተማው የቦታው ልኬት 680 ካሬ ሜትር ነው የሚል ከሆነ በእነርሱ በኩል ለማካፈል ችግር የሌለባቸው መሆኑን አመላክተዋል።

## የተገኘው ውጤት

በመጨረሻ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አቤቱታውን በማስተናገዱ ትልቅ ድል ማግኘታቸውን ለመጠቆም ቢሮ ድረስ የተገኙት ወይዘሮ መድሃኒት እንደተናገሩት፤ ዘገባው በመተላለፉ እና ድርጅቱ በተለይ ፍርድ አፈጻጸም ላይ በመስራቱ እንባቸው ታብሷል። ሌሎች አጭበርብረው እንዳይጫወቱባቸው ረድቷቸዋል።

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት ቤቱን ለማካፈል ሃላፊነት ወስዶ ለሽያጭ የሚቀርበው ቤት 600 ካሬ ሜትር አካባቢ ስፍት ያለው ቢሆንም 500 ካሬ ሜትር በማለት ለመሸጥ ተነስቶ ነበር። በዚህ ምክንያት የሽያጭ ዋጋውም 5መቶ 50 ሺህ ብር አካባቢ ተቆርጦለት ነበር። ሆኖም ለአመታት የኖሩበት ቤት በርካሽ ዋጋ ሊሸጥ መሆኑን ጠቅሰው አቤቱታ በማቅረባቸው ከክፍለ ከተማው የመሬቱ ስፋት ተሻሽሎ በድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ ተደረገ። ቤቱም በ11 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር ተሸጠ።

ወይዘሮ መድሃኒት ፤ ይህ ውጤት የመጣው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አቤቱታ አቅራቢዋ የሰጡትን መረጃዎች ዋቢ በማድረግ ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ጥልቅ ምርመራዎችን በማካሔዱ ነው። በመሆኑም እንባችን እንዲታበስ ትክክለኛውን ፍትህ እንድናገኝ ላደረገን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ታላቅ ምስጋና አቀርባለሁ ብለዋል።

**ከአዘጋጁ**

**የዝግጅት ክፍሉ የምርመራ ዘገባው ይሳካ ዘንድ የፍርድ አፈጻጸም ዳሬክቶሬት ያሳየውን መተባበር በማድነቅ ምስጋናውን ያቀርባል።**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# መኃልየ መኀልይ ዘኢትዮጵያ

**ቀዳሚ ማስታወሻ፤**

ለአንድ መቶ ፐርሰንት ጥቂት ነቁጦች ብቻ ሲቀሩ መላው ሕዝበ ኢትዮጵያ በተለያዩ የሃይማኖቶች ጥላ ሥር መሰባሰቡ የተረጋገጠ እውነት ነው። ስለሆነም ከወቅት ጋር የሚሄዱ ወይንም ከሁኔታዎች ጋር የሚስማሙ ሃሳቦችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እየተዋሱ ርዕሰ ጉዳዮችን ማጎልበት ሊበረታታ የሚገባው እንጂ በፈራ ተባ ሊታለፍ የሚገባ መሆን የለበትም።

የሃይማኖት መጻሕፍት አዘውትረው ሊጠቀሱ የሚገባቸው ለነፍስ ትድግና ዋስትና ስለሚሰጡ ብቻ ሳይሆን ለዕለት ተዕለት የሕይወት ስምሪት፣ ለዕውቀትና ለጥበብ ሀሰሳ ጭምር ፋይዳቸው ከፍ ያለ መሆኑን ማስታወሱም አግባብ እንደሆነ እናምናለን። በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥም ይሄው እውነታ በግልጽነት ተመልክቷል።“የሰው ልጅ ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ቅዱሳት መጻሕፍት ለትምህርት፣ ለተግሳጽ፣ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ሁሉ ይጠቅማሉ” ይላል። (2ኛ ጢሞ. 3፥16)።

ግራ ተጋብቶ እኛን ዜጎችንም ግራ መጋባት ላይ ጥሎ አሳራችንን እንድንባለ የፈረደብን ገዢው ሕገ መንግሥታዊ ሰነዳችን፡- “መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም። ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም” (አንቀጽ 11፥3)፤ በማለት የደነገገው ሃሳብ እንኳን ለእኛ ለተራ ዜጎች ቀርቶ ለሕገ መንግሥቱ “ጠበብትና ፖለቲከኞች” ሳይቀር በትርጉም አሰጣጥና በአፈጻጸም ረገድ ግራ ሳያጋባቸው እንደማይቀር እንገምታለን።

ለመጻፍ ያህል ብቻ ተጽፎም ከሆነ “እፉ” ብለን በአሜንታ እንቀበላለን እንጂ እውነትነቱን አምናችሁ ተቀበሉ የምንባል ከሆነ ግን በሙግቱ ረቺና ተረቺ ስለመኖሩ ያጠራጥረናል። ይኼው ሕገ መንግሥት ለወደፊቱ የሕዝብ ይሁንታ አግኝቶ ክለሳ የሚደረግበት ከሆነ ይህ “የጣልቃ መግባት ያለመግባት” ጉዳይ በአግባቡ እንዲፈተሽ ከወዲሁ ማስታወሻ በማኖር አደራችንን እናስተላልፋለን።

**መነሻና መዳረሻችን፤**

ለዚህ ጽሑፍ የሰጠነውን ርዕስ የተዋስነው “መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን” በሚል ስያሜ ከሚታወቀው የቅዱስ መጻሕፍ አንድ ክፍል ነው። “መኃልየ መኃልይ” ማለት “ከመኃልይ የሚበልጥ መኃልይ” ወይንም “ከመዝሙር ሁሉ የሚበልጥ መዝሙር” ማለት ነው። “የአማልክት አምላክ፣ የጌቶች ጌታ፣ የነገሥታት ንጉሥ ወዘተ.” ከሚሉት ማነጻጸሪያዎች ጋር ማስተያየቱ ለግልጽነት ይጠቅማል።

የቅዳሳት መጻሕፍት ተንታኞች “መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን” የሚለውን ርዕስ የሚያብራሩት በሰሎሞን ወይንም ለሰሎሞን ወይንም ስለ ሰሎሞን የተጻፈ መዝሙር እንደሆነ ነው። ይህንን ማንጻሪያ (Analogy) በመዋስም “መኃልየ መኃልይ ዘኢትዮጵያ” በማለት ለዚህ ጽሑፍ በተዋስነው ርዕስ ለማሳየት የሚሞከረው “በኢትዮጵያ በራሷ” ወይንም ለኢትዮጵያ ወይንም ስለ ኢትዮጵያ ልንዘምር ስለሚገባን ዋና ጉዳይ ስለሆነ አንባቢያን ቀድመው የመነሻችንን ዐውድ በአግባቡ እንዲረዱ በማስታወስ ወደ ዝርዝር ጉዳያችን እናቀናለን።

ለኢትዮጵያ ወይንም ስለ ኢትዮጵያ የተዜሙት፣ የተነገሩት፣ የተወሩትና የተጻፉት የእስከ ዛሬ “መዝሙሮች” ይዘት በአብዛኛው ወደየት እንደሚያተኩር አይጠፋንም። በዚህ ጽሑፍ “መዝሙር” እየተባሉ የሚጠቀሱት ሃሳቦች የግጥምና የዜማ ጠበብት የተራቀቁባቸውን ድርሰቶች ብቻ ማለታችን አይደለም። ዕለት ተዕለት አፋችንን በእንጉርጉሮ የምናሟሽባቸውን፣ በቡድን ውይይትና በቤተሰብ መካከል የምናንሸረሽራቸውን፣ በየሚዲያውና በማኅበራዊ መድረኮች (Platforms) እየጣልን የምናነሳቸውን፣ እያከበርን የምናሞግሳቸውን፣ እያንቋሸሽን የምንተቻቸውንና ግራ በተጋባ ስሜት ውስጥ ስንሆን ስለ እርግጠኝነታቸው ሳንጨነቅ የምንቀባበላቸውን ዘርፈ ብዙ ዝርው ሙግቶችንና ርዕሰ ጉዳዮችን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው።

አንኳር ሃሳባችንን የሚወክልልንን አንድ ጥቅስ የጽፉን ርዕስ ከተዋስንበት “የመኃልየ መኃልይ” መጽሐፍ በመዋስ እንንደርደር፡- “እነሆ! ክረምቱ አለፈ። ዝናቡም አባርቶ አበቃ። አበቦች በምድር ላይ ፈክተው ተገለጡ። የዜማም ጊዜ ደረሰ። የርግቦች ድምጽም በምድራችን ተሰማ” (ምዕ. 2፥11-12)።

በማንኛውም ቋንቋ ውስጥ ለቃላት ፍቺ የሚሰጠው አንድም በእማሬያዊ አለያም በፍካሬያዊ ይዘታቸው ነው። እማሬና ፍካሬ የሚሉት ሁለቱ ቃላት ምንጫው የግዕዝ ቋንቋ ነው። እማሬ የሚወክለው ያልተሰወረውን ግልጽ ፍቺ ወይንም የመዛግብተ ቃላት “ጥሬ ትርጉምን” ሲሆን በአንጻሩ ፍካሬ የሚወክለው ከጥሬ ትርጉሙ በስተጀርባ ያለውን ሰፊና ጥልቅ ሃሳብ ይሆናል።

በዚሁ መሠረትም ከላይ ከፍ ብለን ከጠቀስነው የመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ የጠቀስነው ጥቅስ በሁለቱ የአተረጓጎም ስልት መሠረት ከሀገራዊ ጉዳዮቻችን ጋር እያስተያየን እንፈትሻለን። ክረምት የሚወክለው ከሰኔ 25 እስከ መስከረም 26 ያሉትን የዝናብ ወቅት ብቻ አይደለም። “ክረምት” በአንዳንድ ባህሎች በፍካሬያዊ ትርጉሙ የሚወክለው ከፍተኛ ችግር በተጋረጠ ወቅት የስሜት ህመም ጠንክሮ እንባ እንደ ውሃ በጉንጭ ላይ የሚታፈስበትን ጭጋጋማ የመከራና የሀዘን ቀናትን ነው። አበቦችም የብሩህ ተስፋ ምሳሌዎች ናቸው። ርግብ የሰላም መገለጫ ምልክት (Symblole) መሆኗም በሁሉም ዘንድ የታወቀ ነው።

ይህን መሰሉን ግርድፍ የቃላት አተረጓጎም መነሻ በማድረግ ከሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ አንዳንድ ሁኔታዎች ለመቃኘት እንሞክር። የእስከ ዛሬው የሀገራችን ታሪክም ሆነ እያዜምን ያደግናቸው መዝሙሮችም ሆኑ ትርክቶች በጦርነትና በጦረኝነት የደመቁ መሆናቸው ለክርክር አይጋብዝም። በግፈኞች ሰለባ ደማቸው ከንቱ ፈሶ የቀረ የዜጎቻችን ቁጥርም ከ እስከ ተብሎ በአሀዝ የሚገለጽ አይደለም።

እነዚህን መሰል “በክረምት የሚመሰሉ” ነባር ታሪኮቻችን ችግሩን ትርክቶቻችንን ለጊዜው አቆይተን በወቅታዊ የሀገራችን መከራ ላይ ብናተኩር እንኳን ለአስረጂነት የሚመጥኑ በርካታ ክስተቶችን አስተናግደንና እያስተናገድን ስለሆነ ወደ ሩቅ ዓመታት ታሪኮቻችን መንጠራራቱ እጅግም ለመነሻችን ቅርበት ላይኖረው ይችላል።

“ዛሬ” በምንለው ጀንበራችን ኢትዮጵያ ምን ያህል መከራዎችን ተሸክማ እየቃተተች እንዳለ የምናየውና የምንሰማው ነው። መዝሙሮቻችንም ሆኑ ውይይቶቻችን፣ ንግግሮቻችንም ሆኑ ምክክሮቻችን ወይንም ጽሑፎቻችን በሙሉ የታጀሉት የሀገርን መከራ በመተረክ ላይ ነው። በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት ከውስጥና ከውጭ የደም ጥማተኞችና ግፈኞች የተፈጸሙብን መልከ ብዙ ጦርነቶች፣ አልቂቶች፣ ዝርፊያዎችና ዘርዝረን የማንዘልቃቸው መከራዎቻችን ኢትዮጵያን “ጥቁር ከል” ያስለበሱ፣ ሕዝቡን ለመፈናቀል፣ ለሥነ ልቦና ቁስልና በቀላሉ ሊሽር ለማይችል ስብራት የዳረጉ እንደነበሩ አይዘነጋም። ዛሬም ከመሰል መከራዎቻችን ነፃ ወጥተናል ብለን ለመፈንጠዝና “የአሳሮቻችንን ዝተት” አውልቀን የመጣል ደረጃ ላይ ደርሰናል ብለን አንፎክርም።

2014 ዓ.ምን ሸኝተን 2015 ዓ.ምን የተቀበልነውም የሀዘን ድባባችን ተገፎ፣ የጦረኞቹ ጠላቶቻችን የጠብ መንጃ ልሳን ተዘግቶ “በሃሌሉያ” ዝማሬ እያሸበሸብን ነው ማለትም አይደለም። በርእሰ ዐውዳመታችን ዕለት እንኳን ሳይቀር ከታዳጊ ልጆቻችን “የአበባ አየሽ ወይ” ዜማ ይልቅ ጎልቶ ሲደመጥ የነበረው “ጀግኖቻችን ዛሬስ የትኛውን አካባቢ ነፃ አውጥተው የምሥራች አሰሙን” የሚሉ “ዜናዎችና” ትንተናዎች ላይ ልባችንንና ቀልባችንን ሙሉ ለሙሉ ሰጥተን ነበር።

**“እሰይ ደስ ይበለን“ ከሚል የምሥራች ገላጭ ዜማ ይልቅ ጎልቶ ይደመጥ የነበረው፡-**

**“የሀገሬ ጀግኖች ሴት ወንዱ ታጠቁ፣**
**ከእንግዲህ ስጠላት አንተኛም ንቁ።**
**ጀግንነት እንደሆን የአባቶቻችን ነው፣**
**ኅብረታችን ጸንቷል ድል መምታት የእኛ ነው።”**

እንዳለው ዜመኛው በቁጭት እንጉርጉሮ እያዜምን ነበር። ድል ለጀግኖቹ የመከላከያ ልጆቻችንና እንደ ተርብ ተናዳፊ ለሆኑት የጥምር ጦሩ አንበሶች ይሁንና በአዲስ ዓመት ዋዜማና መባቻ ቀናት እጅግ የሚያስገርሙና የሚያስፈነጥዙ የድል ብሥራቶችን እየሰማን ነው። አድማ የጠሩብን መንግሥታት ሳይቀሩ “እውነታው ቢተናነቃቸውም” የጨፈገገው ፊታቸው ፈታ የማለት አዝማሚያ ያሳየበትና አንዳንዶችም በሚሰሙት ታላላቅ ሀገራዊ ደማቅ የድል ዜናዎች “ጆሯቸው ጭው ብሎ” ግራ የተጋቡበት ቀናት ነበሩ። የእኛ ሀገራዊ መኃልይ በድል መዓዛ ሲታወድ የጠላቶቻችን ጠረን ደግሞ የተግማማ ወደ መሆን ደረጃ እየተቀየረም ይመስላል።

ለእኛ ለኢትዮጵያዊያንና ለውዷ ሀገራችን “የመከራችን ክረምት” እየጠባ፣ የተስፋችን መገለጫ አበቦችም እየፈኩና የቆሰለችው የሰላማችን ርግብ ወደ ፈውስ እየተቃረበች እንዳለች በድሉ መኃልየ መኃልይ እየተረጋገጠልን ነው። ድሉ ወደ መቋጫው እየተንደረደረ እንጂ የታመመችው የሰላም ተምሳሌቷ ርግባችን በአየ ራችን ላይ መኃልያችንን እያስተጋባች በሙሉ አቅሟ ለመብረር ገና የማገገሚያ ወራት ያስፈልጋታል።

ቢሆንም ግን በፈጣሪ ቸርነት በተቀበልነው የ2015 ዓ.ም ዜማችን የሰላም፣ ቋንቋችን የሰላም፣ ንግግራችን የሰላም ሆኖ አየሩን ብንፈውሰው ኑሯችንና ሕይወታችን በአጭር ጊዜ ተፈውሶ ሀገራዊ እንቆቅልሾቻችን በሙሉ እየተፈቱ ለመተርተር ይፋጠኑ ነበር።

ሀገራችንን የከበበው የጥፋት ደመና እየተገፈፈ፣ አየራችንን የበከለው የክፉዎች መርዝ እየተጠረገ የጦርነት ወሬዎች ታሪክ ለመሆን የተቃረቡ ይመስላል። ስለዚህም ኢትዮጵያ በራሷ አንደበት የምትዘምረው መኃልይ፣ ወይንም ስለ ኢትዮጵያ የሚቀነቀነው መዝሙር፣ ወይንም ለኢትዮጵያ የሚደረሰው ዜማና ግጥም ሰላምን የሚያሞግስ እንጂ በቂምና በቁርሾ የጠለሸ ሊሆን አይገባውም።

ንግግሮቻችን፣ ጽሑፎቻችን፣ ውይይቶቻችንና ምክክሮቻችን ሁሉ ሰላምን የሚያደምቁ፣ ስለ ሰላም አሸናፊነት የሚሰብኩ እንጂ ዳግም ሰላምን ጥቁር ቱቢት አስለብሰው የሀዘን ፍራሽ ላይ ኀዝጉዘን እንድንቀመጥ የሚጋብዙ መሆን የለባቸውም።

የዜማችን አስኳል መልእክት ቀደም ሲል የጠቀስነው የመኃልየ መኃልይ ሃሳብ ሊሆን ይገባል። ደግመን እናስታውሰው፡- “እነሆ! ክረምቱ አለፈ። ዝናቡም አባርቶ አበቃ። አበቦች በምድር ላይ ፈክተው ተገለጡ። የዜማም ጊዜ ደረሰ። የርግቦች ድምጽም በምድራችን ተሰማ።”

ከዜማችን በማስከተልም የኢትዮጵያን ፊት ሙሉ ለሙሉ ወደ ልማት ማዞር፣ እኛም ልጆቿ እጆቻችንን ለኅብረት ስራ ማጠናከር ይኖርብናል። በሌላኛው የቅዱስ መጽሐፍ ክፍል እንደተጠቀሰው፡- “ጠላቶቻችንም መልካም እንደሆነልን፣ ፈጣሪም ምክራቸውን ከንቱ እንዳደረገ ሰሙ። እኛም ሁላችን ወደ ሥራችን ተመለስን” በማለት በኢትዮጵያ አየር ላይ ዝማሬያችን ሊናኝ ይገባል።

እስከ ዛሬ ብዙ ተቸን፣ ጻፍን፣ ዘመርን፣ በክፉ የሀሜትና የመናናቅ ቃላት እርስ በእርስ ተቋሰልን። አሸናፊና ተሸናፊ በሌለበት እንካሰላንትያ እየተጠዛጠዝን ለልጆቻችን ክፋውን፣ ለታሪክም ትዝብት አተረፍን እንጂ ምንም አልፈየደልንም። ስለዚህ በፈጣሪ ቸርነት በተቀበልነው በዚህ “አዲስ” ዓመት ለኢትዮጵያ የምንቀኝላት መኃልይ የሰላም ቅኔ ሊሆን ይገባል።

ቀልባችንን አስክነን፣ ብሽሽቁን አቁመን፣ ፉከራውን ገታ አድርገን ስለ ሰላም ብቻ እንጻፍ፣ እንደስኩር፣ እንሟገት፣ እንማማር፣ እንቀባበል። “ክረምታችን አልፏል፣ አበቦችም ተገልጠዋል፣ ሰላማችንም በቅርቡ ይረጋገጣል” ኢትዮጵያም የሀዘን ጨርቋን አውልቃ የሙሽርነት የማዕረግ ልብሷን ትጎናጸፋለች። ልጆቿም ለሉዓላዊነቷ ክብር፣ ለእድገትና ብልጽግናዋ እጅ ለእጅ ተያይዘው በመሥራት በዓለም ፊት ደምቀው ይወጣሉ። ይኸው ነው። ሰላም ይሁን።

# ከአነስተኛ ምርትና ገበያ ወደሰፊው እየተሸጋገረ ያለው የማር ሀብት ልማት

ስምስም መንግሥቱ

የአዳራሹ በተለያዩ ምርቶች ተሞልቷል፤ ሚሊኒየም አዳራሽ። ጤፉ፣ ጥራጥሬው፣ የቅባት እህሉ፣ አትክልትና ፍራፍሬው፣ የማርና ሰም ምርቱ፣ በፋብሪካ ከተቀነባበሩት ፓስታና መካሮኒ፣ ዱቄት፣የተለያዩ ብስኩቶች፣ወተትና የወተት ተዋጽኦ፣ ከአልኮል መጠጦችም ወይንን ጨምሮ በርካታ ምርቶች በስፋት ቀርበዋል።

ከግብርና ምርቶች በተጨማሪ አልባሳትና ሌሎች የፋብሪካ ውጤቶች በአንድ ቦታ መቅረባቸው አምራቹንና ሸማቹን ማገናኘት የተቻለበት አጋጣሚ ማለት ያስችላል። አጋጣሚው ለበዓል ወቅት ብቻ የሚጠቅም አልነበረም፤ የአንድን ተቋም አገልግሎት ወይንም ጥራት ያለው ምርት ፈልጎ ግን ደግሞ ለማግኘት ለተቸገረ ሸማች ሁሉንም አይነት አገልግሎቶች በአንድ ስፍራ ማግኘት ያስቻለም ነው።

ለግብርናው ስራው ግብአት የሚሆኑ አነስተኛና ከፍተኛ መጠን ያላቸው ማሽነሪዎች፣ ማቀነባበሪያዎች፣ ፀረተባይ ኬሚካሎችም እንዲሁ ለሽያጭ ቀርበዋል።

ቀኑ ጳጉሜን 2 ቀን 2014 አም ነው። ይህ ቀን የአምራችነት ቀን በሚል ተሰይሞ አምራችነት በተለያዩ ዝግጅቶች የተከበረበት ነው። በአዳራሹ ከክልሎች፣ ከአዲስ አበባ ከተማና ዙሪያዋ የመጡ አምራቾችና አልሚዎች ምርትና አገልግሎታቸውን ይዘው ቀርበዋል። ሸማቾችም የመድረኩ ተቋዳሾች ነበሩ፤ አምራቾቹ ምርቶቻቸውንና አገልግሎቶቻቸውን በማስተዋወቅ ደንበኛ ለማፍራት የሰሩበት፣ ሸማቾችም የተለያዩ ምርቶችን ጥራታቸውን እያረጋገጡ የገበዩበት። ወቅቱ የበዓል መዳረሻም ስለነበር አምራችና ሸማቹ የተገናኙበትት መልካም አጋጣሚ መሆን ችሏል።

በዚህ የአምራቾች ቀን መድረክ አምራችና ሸማቹ ብቻ አይደለም የተገናኙት፤ መርሃ ግብሩን ያዘጋጁት ስድስት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ተገኝተዋል፤ እነሱም እንደ ቡናና የመሳሰሉትን ምርትና አገልግሎታቸውን አስተዋውቀዋል። ሚኒስትሮችና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችም ዝግጅቱን በመጎብኘት፣ እዛው መቅመስ የሚቻለውን በመቅመስ አምራቾችንና አገልግሎት ሰጪዎችን አበረታትተዋል።

በዚህ የአምራችነት ቀን ላይ ለሥራ በተገኘንበት ወቅት በተለያየ የኪሎ መጠን ታሽጎና የምርት መለያ ተለጥፎበት (ሌብል ተደርጎ) ከገጠር ተጓጉዞ በስፍራው የቀረበ ማር ተመለከትን፤ እንዲህ ያለው አቅርቦት አልፎ አልፎ እንደ ሱፐርማርኬት ባሉት የግብይት ማእከላት ውስጥ እየተለመደ መጥቷል። የማር ምርቱ በዚህ አይነት መልኩ ለሽያጭ መቅረቡ የግብርና ምርቶችን እሴት ጨምሮ ለሸማቾች የማቅረብ ባህል እየዳበረ መምጣቱንም ያመለክታል።

ከከተማ ወጣ ባለ የገጠር አካባቢ ከሰፈፉ የተለየ ወይም የተጣራ ማር ታሽጎና የምርት መለያና ስያሜ ይዞ እንዲቀርብ መደረጉ የማሩ ሰፈፍ/ሰም/ ም ለብቻው ተዘጋጅቶ ለገበያ ምቹ በሆነ መልክ መቅረቡ ትኩረታችንን ሳበው። በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍል ማር ከነሰፈፉ ሲሸጥ የተመለከተ በአዳራሹ የቀረበው የማር እና ሰፈፍ ግብይት በማርና ሰፈፉ ምርት ግብይት ላይ ለውጥ እየመጣ መሆኑን እንዲገነዘብ ያስችለዋል።

ማሩ እና ሰሙ የተመረተው በአማራ ክልል አዊ ዞን ጓጉሳሽኩዳድ ወረዳ ሽንኩርታ ቀበሌ ናንታ ጎጥ ነው፤ አምራቾቹ ደግሞ በንብ ማነብ ወይንም በማር ልማት በማህበር የተደራጁ ወጣቶች ነው። የማምረት ስራው 13 ሴቶችና ሁለት ወንዶች በመሆን ትግሥት፣ላወይ፣መሰለችና ጓደኞቻቸው ብለው በሰየሙት ማህበር ነው የሚከናወነው።

የማህበሩ ሰብሳቢ ወጣት ትግሥት ተስፋሁን እንደነገረችን፤ በአዲስ አበባ በተዘጋጀው መድረክ የሚቆዩት ለአጭር በመሆኑ መጠኑ አነስተኛ የሆነ ምርት ነው ይዘው የቀረቡት። ማህበሩ ምርቱን እንዲያስተዋውቅ የተፈጠረለት ምቹ ሁኔታ በቀጣይም ሰፊ የገበያ ዕድል እንደሚያስገኝለት ተስፋ አድርጓል። አባላቱ ባቀረቡት የማር ምርት ሸማቹ መርጧቸው ባለበት ቦታ ሆኖ ምርታቸውን ለማዘዝ እንዲችል የሚያደርግ በጥራት የታሸገ ማር ይዘው ነው የቀረቡት።

አካባቢያቸው ለማር ልማት ምቹ እንደሆነ የምትናገረው ወጣት ትግስት፣ ከተሰራ በስፋት ማቅረብ የሚቻልበት ዕድል መኖሩንም ትገልጻለች። የማህበሩ አባላትም የሥራ ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሳ፣ የሚመጣውን የገበያ ፍላጎት ለማሟላት ዝግጁ እንደሆኑም ገልጻለች።

እርሷ እንዳለችው፤ አባላቱ በማህበር ተደራጅተው ወደ



በንብ ማነብ በማህበር የተደራጁ ወጣቶች እሴት የተጨመረበት የማርና ሰም ምርት ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ

ሥራ ከገቡ ሁለተኛ አመታቸውን ይዘዋል፤ ውጤታቸውን ለማየት ጓጉተዋል። እስካሁን ባለው ተሞክሮ የማር ልማቱ በአመት ሁለቴ ነው የሚከናወነው። እነሱም በህዳርና በግንቦት ወራት ሶስት መቶ ኪሎ ግራም ማር አምርተዋል። ይሄን ሥራ በማሳደግ ከዚህ በላይ በማምረት ገበያውን ለመያዝ እየሰሩ ናቸው። ምርቱን ለማሳደግና ጥራት ያለው ማር ለማምረት ንቦችን በተገቢው መንገድ መንከባከብ፣ የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ፣ የሚቀስሟቸውን እጽዋት በስፋት መትከል ይጠበቃል። ይህን ማሟላት ከተቻለ ንቦች ከፍተኛ የማር ምርት መስጠት እንደሚችሉ በአንድ አመት የንብ ማነብ ሥራ ተሞክሮ አግኝተዋል።

ወጣቶቹ በዘመናዊ የማር ማቀነባበሪያ ተጠቅመው ከእጅ ንክኪ ነፃ የሆነ የማር ምርት ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ። ከከተማ ወጣ ባለ አካባቢ የሚኖሩ በመሆናቸውና በማህበር ተደራጅተው ወደ ሥራ ከገቡም ገና አጭር ቆይታ ያላቸው እንደመሆናቸው ምርቱን የሚያቀነባብሩበትን ቴክኖሎጂ እንዴት ማግኘት እንደቻሉ ላቀረብንላቸው ጥያቄ ወጣት ትግስት ስታብራራ እንዳለችው፤ የሥነ ነፍሳት ምርምር ማዕከል ሞይሽ ፕሮጀክት(ኢሲፔ) በቅድሚያ ስለንብ ማነብ፣ ማር ቆረጣና ዘመናዊ አስተሻሸግ፣ በተግባር የተደገፈ ስልጠና ሰጥቷቸዋል።

በዚህም ክህሎት መጨበጥ እንዲችሉ ከተደረገ በኋላ ዘመናዊና የተሻሻሉ ቀፎዎችን እና በማር ቆረጣ ወቅት የሚያስፈልጉ አልባሳትን በማቅረብ ፣ማሩን ከሰፈፉ ለይቶ የሚያጣራና የተጣራውንም ማር በማሸጊያ እቃ ውስጥ ለመጨመር የሚያስችል መሳሪያ እንዲሁም ለማሩ ማሸጊያ ዕቃ በማቅረብ ለማር ልማቱ አስፈላጊ የሆነ ቁሳቁስ ከተሟላላቸው በኋላ ነው ወደ ልማቱ የገቡት። ያሉበት ወረዳም ንቦች የሚቀስሙትን እጽዋት የሚያለሙበትን ቦታ አመቻችቶላቸዋል፤ ይህን ድጋፍ በጋራ ተጠቅመው ለውጤት በቅተዋል።

እንዲህ ያለው የፕሮጀክት ድጋፍ ለተወሰነ አመት ብቻ የሚዘልቅ እንደሆነ ይታወቃል።ባለው ተሞክሮ ፕሮጀክቶች ውስን ጊዜያቸውን ጨርሰው ሲወጡ እንቅስቃሴው ባለበት የማይቀጥልበት ሁኔታ ይስተዋላል። ወጣት ትግስት የፕሮጀክቱ ድጋፍ ለአምስት አመት ብቻ እንደሚቆይ አባላቱ ግንዛቤው አላቸው ትላለች። ፕሮጀክቱ ክህሎት እንዲጨብጡ በመደረጉም ለማር ልማቱ የሚውል የተለያዩ የመሥሪያ ግብአቶችን ስላሟላላቸውና የመስሪያና የመሸጫ ቦታም ገንብቶ ስለሰጠላቸው፣ ለንብ ማነቢያ የሚሆን መሬትም በወረዳው ትብብር ተደርጎላቸው ስለተሟላላቸው ከዚህ በኃላ ወደኃላ የሚመለሱበት ሁኔታ እንደሌለ ተናግራለች። በእነዚህ ድጋፎች የበለጠ አቅም ፈጥረው የማር ምርታቸውን ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ጭምር መዘጋጀታቸውን ነው የጠቆመችው።

እነ ትግስት የገበያ ዕድላቸውን አስፍተው አካባቢያቸውን በማር ምርት ለማስተዋወቅ ጭምር አቅደዋል። ፕሮጀክቱ የጊዜ ገደቡን አጠናቅቆ ሳይወጣ ውጤቱን ለማሳየት ተግተው እየሰሩ እንደሆነም ነው ወጣት ትግሥት የተናገረችው። ከማር ልማቱ ጎን ለጎንም ለእድገት የሚያበቁ ሥራዎችን ለመሥራትም አቅደዋል። ለእዚህም የሥራ ተነሳሽነታቸው ከፍተኛ መሆኑን ነው ከወጣት ትግስት አገላለጽ መረዳት የቻልነው።:

በምርት መጠን ማነስ፣በጥራት መጓደል፣በዘመናዊ መሣሪያ የታገዘ የተጣራ ማር ለገበያ ለማቅረብ የክህሎትና የአቅም ውስንነት፣ የማር ምርቱ ለውጭ ለገበያ ቀርቦ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኝ ቀርቶ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን እንኳን ያሟላ እንዳልነበር ምርቱን አስመልክቶ በተካሄዱ የተለያዩ መድረኮች ሲነሳ ይታወሳል። እሴት የተጨመረበት የማር ምርት ለሸማቹ ምቹ ከመሆኑ በተጨማሪ አልሚው ወይንም አምራቹ በገቢ ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆን እንደሚያደርግ ተደጋግሞ የሚነሳ ጉዳይ ነው። ችግሮቹን ብቻ ከማውሳት ባለፈ የማር ልማቱን በማሳደግና የገበያ ፍላጎትን በሚያሟላ መልኩ ለማቅረብ ጥረቶች አልተቋረጡም።

ትግሥት፣ላወይ፣መሰለችና ጓደኞቻቸው ማህበር አባላት ከእጅ ንኪኪ ነፃ የሆነ የጣራ ማር እንዲያመርቱና የገበያ ትስስርም እንዲፈጠርላቸው በማድረግ የማር ምርት በቀጣይም ለውጭ ገበያ ጭምር በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖረው በመንግሥት፣በማስተርካርድ ፋውንዴሽንና የሥነ ነፍሳት ምርምር ማዕከል (ኢሲፒኤ) ትብብር እየተሰራ ይገኛል። መንግሥት ሥራ ፈላጊ ወጣቶችን በማደራጀትና የሥራ ቦታን ምቹ በማድረግ፣ ኢሲፔ ደግሞ ክህሎት፣ለማር ልማት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁስን በማሟላትና የገበያ ትስስር በመፍጠር ማር ለማምረት የተደራጁ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለውጤት እያበቋቸው ይገኛሉ።

የሥነ ነፍሳት ምርምር ማዕከል ሞይሽ ፕሮግራም(ኢሲፔ) ዋና አስተባባሪ ዶክተር ወርቅነህ አያሌው እንደተናገሩት፤ ማር እንደሌላው የግብርና ውጤት ሰፊ ገበያ ኖሮት በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አስተዋጽኦ ማድረግ ቢችልም፣ እየተመረተ ያለው ግን በአርሶ አደሮች ደረጃ መጠኑ አነስተኛ የሆነ ማር ነው፤ ምርቱም የጥራት ጥያቄ በስፋት እየተነሳበት ያለና የገበያ አዋጭነቱም ዝቅተኛ ሆኖም ይገኛል። በዚህ የተነሳ አልሚውም ሀገርም ከዘርፉ ይህ ነው የሚባል ገቢ እያገኙ አይደለም። ሸማቹም ቢሆን የተጣራ ማር ስለማይቀርብለት ፍላጎቱ አልተሟላለትም።

እንደ ዶክተር ወርቅነህ ገለጻ፤ አሁን ላይ የማር ልማቱ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተደራጁ ወጣቶች በስፋት እየተካሄደ ይገኛል። ወጣቱም በአካባቢው ላይ በዘመናዊ የማር ልማት መሳሪያ በመጠቀም ጥራት ያለው ማር አሽጎና ስምም ለጥፎበት ማቅረብ በመጀመሩ በማር ገበያው ላይ ለውጦች መመዝገብ ጀምረዋል። ለውጭ ገበያ መቅረብ የሚችል ከማሩ የተለየ ሰምም በወጣቶቹ እየተመረተም ይገኛል።

እና ምርት ሲባል በትልቅ ግብርና ወይንም በከፍተኛ የኢንዱስትሪ ውጤት ደረጃ ብቻ መጠበቅ የለበትም የሚሉት ዶክተር ወርቅነህ፣ ማርን በአካባቢ ላይ በስፋት አምርቶና እሴት ጨምሮ ከትላልቅ ኢንዱስትሪ ውጤቶች እኩል ለገበያ በማቅረብ ገበያውን መያዝ እንደሚቻል ወጣቶችን በማደራጀት ባለፉት ጥቂት አመታት የተከናወኑት ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩ አመልክተዋል።

ማር በቀላሉ ማቀነባበር የሚያስችል ቴክኖሎጂ በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል መፍጠር መቻሉን፣ የንብ ማነብ ሥራውም በዘመናዊ መንገድ እንዲታገዝ መደረጉን፣ ለንብ ማነብ የሚያስፈልጉ ከአልባሳት አቅርቦት ጀምሮ መሟላታቸውን ዶክተር ወርቅነህ ጠቅሰው፣ ከዚህ በኃላ የሚያስፈልገው የንብ ማነብ ፍላጎት ያለው የሰው ኃይል ብቻ መሆኑን ገልጸዋል። ለማር ማጣሪያ ከሚውለው ማሽን በስተቀር የተቀሩት ለንብ ማነብ የሚያስፈልጉ ቁሳቁስም በአካባቢው ተዘጋጅተው ሊቀርቡ እንደሚችሉም ይጠቁማሉ። ቁሳቁሱን ንብ አናቢዎቹ በተመጣጣኝ ዋጋ ሊያገኙ እንደሚችሉም ተናግረው፣ ሁሉንም በገበያ በማስተሳሰር ከማር ልማቱ ተጠቃሚ የሚሆነውን የሰው ኃይል ማስፋት መቻሉንም ነው ያመለከቱት።

ዶክተር ወርቅነህ በወጣቶቹ እየተመረተ ለገበያ እየቀረበ ያለው የማር ምርት በኤሌክትሮኒክስ ወይንም ኢ ኮሜርስ በሚባለው የገበያ ሥርአት ውስጥ መግባቱንም ይጠቁማሉ። በዚህ መንገድ የገበያ ትእዛዝ ለሚያቀርቡ ደንበኞች ቤታቸው ድረስ ተደራሽ የሚሆንበት አሰራር መዘርጋቱንም ነው የጠቆሙት።

እንደ ዶክተር ወርቅነህ ገለጻ፤ ሺጋ ዶትኮም በሚባለው የገበያ ዘዴ የማር ግብይቱ ተጀምሯል። የማር ምርቱም በዓለም አቀፍ የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያልፍ እየተደረገ ይገኛል። ወጣቶቹ በቀጥታ ለውጭ ባይልኩም፣ ምርቶቻቸውን ተቀብለው በሚልኩ ለዓለም ገበያ መድረስ ችሏል።

ይህ በራሱ ተስፋ ሰጪ መሆኑንና ከዚህ ቀደም ከነበረው ጋር ሲነጻፀር ከፍተኛ የሚባል ለውጥ መኖሩን እንደሚያመለክት ተናግረው፣ መሬቱ፣ ሀብቱና የሰው ኃይሉ ሁሉም በመኖሩ በፖሊሲ በመደገፍ በስፋት ተሰርቶ ለገበያ የሚቀርብበትን ሁኔታ ማጠናከር እንደ ሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ።

በማህበር በመደራጀት በንብ ማነብ ሥራ ላይ ተሰማርተው ማር በማልማትም ሆነ የገበያ ዕድል በመጠቀም የሚያደርጉት እንቅስቀሴ፣ በግላቸው ንብ የሚያንቡ አርሶ አደሮችንም ማነቃቃት መቻሉን ዶክተር ወርቅነህ ይገልጻሉ። ይሄ ደግሞ ጥራት ያለው ማር ለገበያ እንዲቀርብ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል ነው የሚሉት።

ከኤሲፒ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ኢሲፔ በሀገር አቀፍ ደረጃ በማህበር ለተደራጁ ንብ አናቢ ወጣቶች ድጋፍ ያደርጋል፤ በየሽ ፕሮጀክት 10ሺ፣በሞይሽ ፕሮጀክት ድግሞ 60ሺ ወጣቶች በንብ ማነብ ሥራ ላይ ተደራጅተው ተሰማርተዋል፡፡ በትግራይ ክልል የሚካሄደው ተመሳሳይ ፕሮጀክት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተከሰተው ጦርነት ምክንያት ቢቋረጥም፣ በአማራ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች በሚደረጉ የተለያዩ ድጋፎች ሰፋፊ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## ዘመኑን ለዘመነኞቹ

ተገኝ ብሩ

ዘመን ዘመንኛውን ይመስላል። በዘመኑ የሚኖሩትን ይስተካከላል። ዘመን የአንድነት መንፈስ የሞላበት መተባበርና ፍቅር ያየለበት ከሆነ፤ ያ ዘመን በፍስሀ ይሞላል። ዘመኑ ሰላም የሰፈነበት እና የፍቅር ከሆነ ያንኑ ይመስላል። ዘመኑ ብሩህ ከሆነ ትውልድም የሚደሰትበትና ሀገር የምትለወጥበት ይሆናል። በተቃራኒው ደግሞ የዘመኑ ባለቤቶች ዘመኑን ካበላሹት ያ ዘመን ጭለማ የወረሰው ይሆናል። አልፎ ሲያስቡት የሚቀፍ፣ ሲነግሩት የማይመች ክፉ ዘመን የሚል ስም ይተርፈዋል።

የዚህ ዘመን ትውልዶች የዚህ ዘመን ባለቤቶች ነን። ስለዚህ የዘመኑ ማማርም ሆነ መንተብ ተወቃሾች እኛው ነን። ስለዚህ ዘመኑን ማንፃትና የተዋበም ማድረግ የእኛ ፋንታ ይሆናል። የዚህ ዘመን ዋነኛ ባለቤቱ የዘመኑ ትውልድ፣ በዚህ ወቅት የተገኘን ሁላችንም ነን። በተለይም የዚህ ዘመን ዋነኛ ተዋናይ የሆነው ወጣት፤ ዘመኑ በሰላም እንዲኖር ሊፈቀድለት ይገባል።

አዎን! በተለይ የወጣቱ ውብ ጊዜ በወጉ ሊኖረው ይገባል። የአገሩን አንገት ቀና ለማድረግ በጉልበቱ ሊለፋላት ይገባል፤ ሮጦ ለሀገሩ ለውጥ ሊያመጣ፣ ጥሮ ህዳሴዋን ሊያረጋግጥ ግዴታ አለበት። እናም ዘመኑን እሱ በሚቃኘው በራሱ ልኬት ሊሰምርለት ያስፈልጋል። ይህ ዘመን የዘመኑ ትውልድ ነውና ራሱ በፈቀደው መልክ እንዲኖረው ለእርሱ እንተውለት።

ለፀብና ለእርስ በርስ ቁርሾ ምክንያት ሲሆን የቆየው የፖለቲካ ልምዳችን ዘመኑን አንትቦብናል። እንደ ኢትዮጵያ ትልቅነት ያልተለቀው የፖለቲካ ልምድ ውድ ጊዜያችንን አለዝቦብናል። የማይጨበጥ የከረመ ቅዠት ዘመናችንን አጨፍግጎታል። ለአገርና ለወገን የምንሰራበት ምርጡ ዘመናችንን በከንቱ ባክኗል። ጥሩ ጊዜያችን እንዲነጠቅ አንፈቅድም። እሳቤያቸው ኢትዮጵያ ካልሆነች፤ መዳረሻ ግባቸው ኢትዮጵያን ከፍ ማድረግ ያልሆኑ ሰዎች ከጨዋታው ገልል ይበሉ። አዲሱን ዘመን በአዲስ መንፈስ እንጀምረው።

የሀገራችንን ህዳሴ እንሻለን የኢትዮጵያን ብሩህ መሆን እንመኛለንና፤ አካሄዳችሁ ይገራ። ተማርን የምትሉ ልሂቃን፣ ፖለቲካውን ለኛ ተው እንደ ጉድ እናሾረዋለን የምትሉ የዘርፉ ተዋናዮች እባካችሁ ዘመናችሁን ኖራችሁ ስታበቁ የእኛን ዘመን አትቀሙን። መልካሙን አመላክቱን በስህተት ውስጥ ዘመናት ያለፈችው ኢትዮጵያ ዳግም የስህተት መኖሪያ አታድርጓት።

አዎ! ይህ ዘመን የእኛ ነውና ለእኛ ተውልን። ዘመኑን ኖሮ የሌሎችን ውድ ጊዜ የሚቀማ፤ እሱ የምሩን ኖሮ ሌላውን የውሸት ለማኖር የሚተጋ ለእኛ በጎ አይደለምና እጁን ከላያችን ላይ ያንሳ። ወጣቱ የተዋበ ጊዜው እንዲበላሽ የወደፊት ተስፋው እንዲጨልም አይፈልግም።

ብሩህ ነገር ሊያይ የተዋበ ነገር ሊያይም የሚያስችለው በጎ አስተሳሰብ መውረስ ይፈልጋል። የተሻለ ዘመን እንዲቀርበው መልካም ጊዜ እንዲመጣለት አጥብቆ ይመኛል። ውብ ጊዜ በጥላቻ ትርክት ማጣት በእርስ በርስ ግጭት ማበላሸትን አይፈቅድም። የሚነገረው በጎ፤ የሚወራለት በጎ መሆን ይገባዋል። ተነስ በታሪክ የከበረችው ሀገርህን ለውጥ እንጂ ተነስ የተከፋችውን ሀገርህ አፍርስ የሚል አይፈልግም። ዘመንህን አጨልም የሚል ጨለምተኛ ሀሳብ ሊቀርብለት አይገባም።

የትውልዱን ውብ ጊዜው ለመቀማት፣ ውድ የሆነውን ዘመኑን ለመንጠቅ የሚሞክር ፖለቲከኛ የራሱን ዘመን አበላሽቶ የዚህ ዘመን ፍካት ላጠልሽ የሚል ስግብግብ ሊቆጠብ ይገባል። ወጣቱ አገሩ በልፅጋ፣ ህዝብ ተለውጦ ማየትን ይመኛል። ለዚህ ምኞቱ መሳካት ለመልካም ሀሳቡ ሙሉ መሆን ደግሞ አብሮነት ሊሰበክ አንድነት ጠቀሜታው ሊነገረው ይገባል።

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ዋናውን ሚና የሚጫወቱት ኤሊቶች፤ ለዘመኑ ባለቤት ወጣት መልካምን ማመላከት ለጥሩ ነገር መጣራት አብሮነትን መስበክ ሲገባቸው በተቃራኒው ሊያቆሙት ሲሞክሩ ይታያል። የሀገር ግንባታ ዋንኛ ተዋናዩን ወጣት አስበው የእርሱን ዘመን ለራሱ በሚሆን መልኩ እንዲኖረው መፍቀድን አለመዱም። ባለፈ ታሪክ የሚጋጭ፣ ባልኖረበት ዘመን የሚጠየቅ ፣ በማያውቀው የሚሳቀቅ ለማድረግ በብርቱ ይሰራሉ።

ይህ መንገድ የተሳሳተ ዘመኑና ባለዘመኑን ትወልድ የማይመጥን ነውና የወጣቱን ዘመን መቀማቱ የተዋበ ጊዜውን መንጠቁ ሊያቆሙ ይገባል። ትውልዱ አብሮነት ገብቶት፣ ተከባብሮና ተማምኖ የሚኖር ጥላቻን ንቆ ፍቅርን አንግሶ ዘመኑን በሰላም የሚያሳልፍ ውብ ጊዜውን በራሱ ቅኝት የሚራመድ መሆኑ ሊታወቅለት ግድ ይላል። ሁሉም የራሱ የሚለው ውድ ጊዜ የኔ የሚለው ዘመን አለው። ወጣቱም እራሱና አገሩ የሚለውጥበት ትኩስ ጉልበቱ ሳይባክን ውጤታማ በሆነ ጉዳይ የሚያውልበት የእድሜው ዋንኛው ክፍል ነውና ዘመኑን ይኑረው።

ሀገር የምትገነባበት ህዝብ የሚለወጥበት መንገድ ማመላከት የወደፊቱ ዘመን ብሩህ እንዲሆን መስራት ሲገባቸው የወጣቱን ዘመን የሚያጨልሙ መልካም ጊዜውን የሚነጥቁት ማነሳሻዎች በርክተዋል። የተሻለች አገር መስርቶ የእራሱ የሆነውን ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ትወልድ፤ ለእነሱ ጉዳይ ሳይሆን መሰላል የፍላጎታቸው ማሚያ ለማድረግ ይጥራሉ። ለወጣቱ የሚሆን ብሩህ ጊዜውን በሰላም የሚኖርበት እድሉን የሚነጥቁት ሀሳቦች እንዲላበስ አጉል እኔ ላንተ ተቆርቋሪ ነኝ፤ ስላንተ እኔ ተሚጋች ነኝ የሚል ማታለያ ያቀርቡለታል።

ወጣቱ እኔ በዘመኔ በፍቅር ማደር በወቅቴ ተስማምቶ መኖር እሻለሁና አስማሙኝ፣ ጥንት አባቶች የነበሩበት አንድነት አብረው ያደሩበት መቻቻል አስተምሩኝ ሊል ነው የሚገባው። እነሱ በተቃራኒው የሚነግሩት አሉታዊ ነገር የሚያስረዱት የተዛባ ሆኗል። ወጣት ሆይ ከዛሬ ምናምን አመት በፊት እነ እንትና አባቶችህ በድለዋልና ተነስ ተዋጋ፤ ወገኔ ሆይ እነ እንትና ሊያጠቁህ ከጫፍ ደርሰዋልና ጠላት ሁናቸው የሚሉ ማታለያዎች አይፈልግም።

ይህ ዘመን መልካም አስተሳሰብ የሚያሸንፍበት የማያሻግር አመለካከት የሚከስምበት ነው። አዎን ይህ ዘመን ዋንኛ ባለቤቱ የዘመኑ ትወልድ ዋንኛ ተዋናዩም የዛሬው በፍቅር ያመነ ዜጋ ነው። ይህ ፈፅሞ ሊቀማ አይገባውም። ወጣቱ ስለ አገሩ መልካም መሆን በርትቶ የሚሰራበት ቀድማ ጀምራ ኋላ የቀረችው አገሩ ወደፊት እንድትራመድ ትኩስ ጉልበቱ ሳይሰስት የሚሰዋበት ዘመኑ ነውና ይህ ዘመን ሊቀማ አይገባም።

የዚህ ዘመን ትውልድ የራሱ የሆነ ጊዜው በፍቅር ያመነ በአንድነት የፀና ሆኖ እንዲያሳልፈው የምትሰብኩት ፍቅር የምትነግሩት ደግሞ አብሮነት መሆን ይገባዋል። ድንቅ የሆነ ዘመኑ ተቀምቶ ባልኖረበት ዘመን ታሪክ የሚጋደል ባላየው ሁነት የሚጋጭ መሆን ከቶም የለበትም። ለዚህ ትውልድ ይህ ዘመን ምትክ የሌለው የተዋበ መልካም ነገሮችን የሚያልምበት ተስፋው እንዲሳካ የሚታትርበት ነውና ዘመኑ ለራሱ ለባለቤቱ ይተውለት። የተሳሳተ ትርክት በማንሳት አትለዩት።

የራሳቸውን አበላሽተው ሲያበቁ የወጣቱ ዘመን ቀምተው መጠለያ ለመስራት የሚያስቡት ፖለቲከኞቻችን ሊያውቁት የሚገባው ትልቅ ቁም ነገር አለ። ዘመኑን የዋጀ የፖለቲካ እሳቤና በአንድነት ቆሞ ጠንካራ ማድረግ የሚችል ሀሳብ እንጂ ወጣቱን ነጣጥሎ በተለያየ ጎራ ሆኖ የሚናቆርበት ሊሆን አይገባም። ከዚህ በተለየ መልኩ የእርስ በርስ ወዳጅነቱ እንዲጠነክር አብሮነቱ እንድጎለብት ሊነግሩት ሊያስተምሩትም ቢጥሩ ለእነሱም እረፍት ለአገሪቱም ብስራት ይሆናል።

የወጣትነት ውብ ጊዜን የሚያጨልሙ ትርክቶችን ማጥፋት የእርስ በርስ ግጭቶችን የሚፈጥሩ ንግግሮችን ማስቆም ይገባል። የወጣቱን ዘመን ለመቀማት የምትፈልጉ የእናንተን በመንገር የእሱን ለመውሰድ ያቀዳችሁ ተግባራችሁ ሊገራ ሀሳባችሁ ሊታደስ ይገባዋል። ወጣቱን ገርታችሁ በአንድነት እንዲቆም፤ አስተካክላችሁ አብሮነቱ እንዲያጠናክር መንገር ከእናንተ ይጠበቃል። ሀገሩን የሚለውጥበት ትኩስ ጉልበቱ በአግባቡ እንዲጠቀምበት፤ይህች ከእርሱ ብዙ የምትጠብቀው እናት ምድሩን እንዲያፀናት ደግፉት። እንዲወዳት አድርጉት። መልካምን በመንገር መልካም ዘመኑን እንዲያቀና ፍቀዱለት።

# ዓለም አቀፍ



## የንግሥቲቷን ሞት ተከትሎ አንቲጓ ሪፓብሊክ ለመሆን ሕዝበ ውሳኔ ልታደርግ ነው

የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የነበረችው አንቲጓ እና ባርቡዳ የንግሥት ዳግማዊት ኤልዛቤጥ ሞትን ተከትሎ ሪፓብሊክ ለመሆን ሕዝበ ውሳኔ ልታካሂድ ነው። የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ጋስቶን ብራዎን ሕዝበ ውሳኔው ከሦስት ዓመታት በኋላ እንደሚከናወን ገልጸው፤ ሕዝበ ውሳኔ የማካሄድ እቅዱ “የጠላትን ድርጊት አይደለም” ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አገራቸው ሪፓብሊክ ብትሆን “ነጻ እና ሉዓላዊ” መሆናችንን የምናረጋግጥበት የመጨረሻው እርምጃ ይሆናል ብለዋል።ንግሥት ዳግማዊት ኤልዛቤጥ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ የአንቲጓ እና ባርባዱ ርዕሰ ብሔር ነበሩ። የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አንቲጓ ሕዝበ ውሳኔ እንደምታደርግ የተናገሩት ንጉስ ቻርልስ ሳልሳዊ የካሪቢያኗ አገር አንቲጓ እና ባርባዱ ርዕሰ ብሔር መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ ነው። ጋስቶን ብራዎን በቀጣይ ዓመት በሚካሄደው ምርጫ ካሸነፉ ሕዝበ ውሳኔውን እንደሚያስፈጽሙ ገልጸዋል።

ንግስት ኤልዛቤጥ ከካረቢያኗ አገር በተጨማሪ አውስትራሊያ፣ ካናዳ እና ኒው ዚላንድን ጨምሮ የበርካታ የቀድሞ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ርዕሰ ብሔር ናቸው። የንግስቲቱ ሞት በአውስትራሊያ ሪፓብሊክ የመሆን እንቅስቃሴን ዳግም አጋግሎታል።

በአሁኑ ወቅት ንጉስ ቻርልስ ሳልሳዊ ከዩናይትድ ኪንግደም በተጨማሪ የ14 አገራት ርዕሰ ብሔር ናቸው። እነዚህም አንቲጓ እና ባርባዱ፣ አውስትራሊያ፣ ባህማስ፣ ቤሊዝ፣ ካናዳ፣ ግሬናዳ፣ ጀማይካ፣ ኒው ዚላንድ፣ ፓፕዋ ኒው ጊኒ፣ ሴንት ኪትስ እና ኔቪስ፣ ሴንት ሉሺያ እና ዘ ግሬናዲኢስ፣ ሰለሞን ደሴቶች እና ቱቫሉ ናቸው።

ከአንድ ዓመት በፊት ባርባዶስ ንግስት ኤልዛቤጥን ከርዕሰ ብሔርነት አንስታ ተመራጭ ፕሬዚዳንቷን ርዕሰ ብሔር በማድረግ ሪፓብሊክ መሆኗን አውጃ ነበር። ሌላኛዋ የካረቢያን አገር ጀማይካ ገዢ የሠራተኞች ፓርቲ ሕዝበ ውሳኔ አካሂዶ ሪፓብሊክ መሆኑን ለማወጅ ማቀዱን ማስታወቁን ቢቢሲ ዘግቧል።



## ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ለተተኪያቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የእንኳን ደስ አለዎት መልዕክት አስተላለፉ

የኬንያው ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ነሐሴ 3፣ 2014 ዓ.ም በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ላሸነፉት ዊሊያም ሩቶ ለመጀመሪያ ጊዜ የእንኳን ደስ ያለዎት መልዕክት አስተላለፉ። አንጋፋው ፖለቲከኛ ራይላ ኦዲንጋ ቀጣዩ የኬንያ ፕሬዚዳንት እንዲሆኑ ድጋፋቸውን የሰጡት ተሰናባቹ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ትናንት መስከረም 3፣ 2015 ዓ.ም በሚደረገው ቃለ መሀላ ስነ ስርዓት ተገኝተዋል።

ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ይህንን የተናገሩት የአስተዳደራቸውን ቁልፍ ስኬቶች አስመልክቶ በነበረው ንግግራቸው ነው። ባለፈው ሳምንት የኬንያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዊሊያም ሩቶን አሸናፊነት የሚቃወሙ በርካታ አቤቱታዎችን ውድቅ በማድረግ ቀጣዩ ፕሬዚዳንትነታቸውን አፅንቷል።

ኡሁሩ ኬንያታ በስልጣን ዘመናቸው ሃገሪቱ ለውጥ እንዳመጣች በመግለፅ ተተኪያቸው የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከት ቢኖራቸውንም ሁሉንም ኬንያውን በእኩልነት እንዲያገለግሉ አሳስበዋል። ተሰናባቹ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ የአስተዳደራቸው ዘመን ስኬቶች በሚል ከጠቀሷቸው መካከል ማዕከላዊ ስልጣንን ወደተለያዩ ግዛቶች እንዲከፋፈል ማድረግ እንዲሁም ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ አባል እንድትሆን ማስቻል ነው።

ትናንት ማክሰኞ መስከረም 3 ቀን 2015 ዓ.ም የሚደረገውን የስልጣን ሽግግር በበላይነት እንዲከታተል የተመደበው ቡድን በስነ ስርዓቱ ላይ ከ20 በላይ የሃገር መሪዎች መጋባዛቸውን የዘገበው ቢቢሲ ነው።የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም በአዲሱ የኬንያ ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ በዓለ ሲመት ላይ ታድመዋል፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ወልደሕይወት - የ17ኛው ክፍለ ዘመን ፈላስፋ

ግርማ መንግሥቴ

አገራት በተለያዩና ባፈሯቸው ሀብቶች (ተፈጥሯዊም ይሁን ሰው ሠራሽ) ይታወቃሉ። ዜጎቻቸው በሠሯቸው ሥራዎች ወይ ከፍ፤ ወይም ደግሞ ዝቅ ሊሉ ይችላሉ። በጀግኖቻቸው "ሌጋሲ" ታፍረውና ተከብረው ይኖራሉ። ፈላስፎቻቸው ባራመዷቸው ፍልስፍናዎች ይፈረጃሉ። ባላቸው ተፈጥሯዊ አቀማመጥም ሆነ በአየር ንብረታቸው ይለያሉ። ባፈሯቸው ምሁራን፣ ሳይንቲስቶችና ተመራማሪዎችም እንደዛው። በሥነጽሑፍ ሥራዎቻቸው ደረጃ ይወጣላቸዋል። ባይሆን ኖሮ ብዙዎቹን ባላወቅናቸው፤ በቀላሉም ባልለየናቸም ነበር። በቀላሉም አስተምህሯቸውን ባልቀሰምን ነበር።

ሼክስፒር ሲባል ጀርመንን እሚያስብ፤ ሂትለር ሲባል አእምሮው ፈጥኖ አሜሪካዊነቱ ላይ የሚሄድ ... ሰው አለ ለማለት እንደሚቸግር ሁሉ፤ ኤሚል ዞላን እንግሊዛዊ፤ ዊትማንን ፈረንሳዊ ብሎ ደረቱን ነፍቶ የሚሟገት ሰው ማግኘት ይቸግራል። (እዚህ ላይ "ሰው" ስንል የሚመለከተውን ሰው እንጂ ሁሉንም ሰው እያልን እንዳልሆነ ማስታወስ ይገባናል።) ከዚህ የምንገነዘበው የመግቢያ አንቀፃችን ትክክል መሆኑን ነውና እንቀጥል።

በብዙዎች ዘንድ ናይጄሪያ የሳይንቲስቶች ምድር (ላንድ ኦፍ ሳይንቲስትስ) በሚል ትታወቃለች። ይህንን በሚያክል ባለሀብትነቷ ትታወቅ እንጂ የሀብቷ ተጠቃሚ ባለመሆኗም ያንኑ ያህል ትወቀሳለች። "ለምን?» ቢሉ፤ በሙሉ ሊያስብል በሚችል ደረጃ የሷ ባለመሆናቸውና በተለይ የአሜሪካ የምርምር ማዕከላትን ያጨናነቁት ትውልደ ናይጄሪያዊ ሳይንቲስቶች በመሆናቸው ነው። "ምክንያት?" ካሉም፣ ምክንያቱን ለገንዘብ ሲባል ወደ ሰለጠኑት ዓለማት የሚደረግ ስደት ሆኖ ያገኙታል። ወደ ራሳችን እንመለስ።


ኢትዮጵያ ጥንታዊትና የራሷም የሆነ አገር በቀል ዕውቀት ያላት አገር ነች። ምናልባት በብዙ ሁኔታዎች ከፍ ብላ ትታይ ይሆናል እንጂ ከብዙዎች ጋር ስትታይ ደፍረው ከጎኗ ሊቆሙ የሚችሉ አገራት ትንሽ ናቸው። ብልጫዋ፣ ልክ እንደ ዕድሜዋ ሁሉ፣ ብዙ ነው። ያላትን ሀብት ከመቁጠር የሌላትን መቁጠሩ ይቀላል። ያፈራቻቸውን ሙያና ባለሙያዎች ከማሰብ "ምን ያላፈራችው አለ?" ብሎ መመራመር ይቀላል። የዛሬው ባለውለታችን ደግሞ አንዱና ቀዳሚው ኢትዮጵያ ያፈራችው ፈላስፋ ነውና ወደ'ዛው፤ ወደ ወልደ ሕይወት እንሂድ።

በአንድ ግዙፍ ሰብእና በመሸፈኑ ምክንያት ነው መሰል ወልደሕይወት በብዙዎቻችን ብዙም አይታወቅም። ምናልባትም እዛው፣ በአካዳሚው ደብርና አካባቢው ስሙ ሊነሳ ይችል ይሆናል እንጂ፤ በጥቂት ጉዳዩን ፈልፍለው ለማውጣት በሚጥሩ ሰዎች አካባቢ ይጠቀስ ይሆናል እንጂ ..... በአንድ ድንቅ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋነቱ ሕዝብ ያውቀዋል የሚል አቋም የሚይዝ ሰው አይገኝም። አይደለም ሥራዎቹን፣ እስከ እራሱም መኖሩን የሚያውቁ ብዙዎች አይደሉም።

እርግጥ ነው ወልደሕይወት (ምትኩ) የፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ ተማሪ ነበር። ወልደሕይወት በዚሁ በተማሪነትና የዘርዓያዕቆብ ተከታይነቱ (በነካ ጣል ነካ ጣልም ቢሆን) ይታወቃል። በተለይ በእነ ብሩህ ዓለምነህ አካባቢ እንደ አንድ አቢይ ርእሰ ጉዳይ ተወስዶ ተፈትሿል። ከማንም በላይ ደግሞ፣ እንደ እነ ክላውድ ሰምነር (ስለእኝህ ምሁር አዲስ ዘመን፣ ረቡዕ ሐምሌ 27 ቀን 2014 ዓ.ም፣ ገጽ 23ን ይመለከቷል) በውጭዎቹ ዘንድ በሚገባ ይታወቃል። (እስከዛው፣ ሰምነር የዘርዓያዕቆብን ፍልስፍና ከፈረንሳዊው የአውሮፓ ዘመናዊ ፍልስፍና መስራች ሬኔ ዴካርት (Rene Descartes) ሥራ ጋር በማነጻጸር፣ ኢትዮጵያ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የነበራትን ሚና፤ በፍልስፍናው ያላትን ቀዳሚነት ለተቀረው ዓለም አጉልቶ አሳይቷል።የሚለውን መያዙ ጥሩ ነው።)

አርስቶትል የፕሌቶ መምህር እንደ ነበረው ሁሉ፤ የዛሬው ባለውለታችን፣ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው፣ በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን የሕይወት ታሪኩንና የፍልስፍና ሥራውን ብራና ዳምጦ፣ ቀለም በጥብጦ፣ በመጻፍ ያቆየልን ኢትዮጵያዊ አመክኗዊ (rational) ፈላስፋ የሆነው፤ የፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ (1599-1692) ደቀ-መዝሙር ነው። ብሩህ አለምነህ እንደሚነግረን ከሆነ ወልደሕይወት ከዘርዓያዕቆብ ጋር ከ1626 - 1685 ዓ.ም ድረስ ለ59 ዓመታት በእንፍራንዝ፣ ደቡብ ጎንደር አንድ ላይ የኖረ ሲሆን፣ ፍልስፍናንና የሃይማኖት ትምህርትንም ከዘርዓያዕቆብ ተምሯል።

(ብሩህ ዓለምነህ "ለቅዱስ ያሬድ ይህ ዓለም በመላ ልክ እንደ አንድ ትልቅ ማህሌት (ሲንፎኒ) ነው፤ ፍጥረታት ሁሉ



በአንድነት በዜማ የሚያመሰግኑበት ሲንፎኒ፡- ይህም ማለት ቅዱስ ያሬድ ተፈጥሮን የሚገነዘበው በቀለሙ፣ በልስላሴው አሊያም በቅርፁ ሳይሆን በድምፁ ነው - ፈጣሪውን በሚያመሰግንበት ዜማው ነው።ለዚህም ነው "ደምፀ እገሪሁ ለዝናም" (የዝናብ እግሩ ተሰማ) ያለው - ዜማን ከዝናብ ድምፅ ፈልቅቆ ሲያወጣ!!! የ6ኛው ክ/ዘ ባህል እንደዚህም ዓይነት አስደናቂ ሰው ፈጥሯል፡፡" በማለት በአንድ ጽሑፉ ላይ ማስፈሩን ማስታወሱ፣ ቢያንስ ያ ክፍለ ዘመን ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ ጠቃሚ መሆኑን በቅንፍ አስቀምጠን ብናልፍ ጠቃሚ ይመስለናል።)

ወልደሕይወት ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ እንዲሉ እንኳን ባይሆን፤ የአስተማሪውን ፈለግ በመከተል ስመ ጥር ፈላስፋ ለመሆን የበቃ ሰው ነው (እንደ የፍልስፍና መምህሩና የአዲስ አድማሱ አምደኛ ፍቃዱ ቀነኒሣ የዘርዓ ያዕቆብና የተማሪው ወልደሕይወት ሐተታዎች፤ በይዘታቸውም ሆነ በአቀራረባቸው ተመሳሳይነት አላቸው)። ከዚያ በፊት ሁለቱ ተለያይተው ሊጠቀሱ በማይችሉ ፈላስፎች ምክንያት ስለ ዘርዓያዕቆብ ሳያነሱ ማለፍ አይቻልምና ባጭሩ ስለ'ሱ (ከትምህርት ጋር በተያያዘ) አንድ ነገር ብለን እንለፍ።

በትምህርት ላይ አብዮት ያካሄደ፣ የትምህርት አብዮተኛ ነበር። ለዚህም "ዘርዓያዕቆብ አክሱም ላይ ወንበር ዘርግቶ ሲያስተምር "ማጥመቅ' የሚለውን ሃይማኖታዊውን የትምህርት ዓላማ፡ ወገንተኛ ሳይሆኑ "መመርመርና መጠየቅ" በሚለው ተካው፤ "ማነብነብ" የሚለውን የማስተማሪያ ዘዴ ደግሞ "መወያየትና መከራከር" በሚለው ዘዴ ለወጠው። ይሄ ነው የዘርዓያዕቆብ የትምህርት አብዮት!!!" ተብሎ በጥናትና ምርምር ሥራዎች ውስጥ የተጠቀሰለትን ማየት ነው። (እዚህ ጋ ከሶቅራጥስ የማስተማር ዘዴ (ሶቅራቲክ ሜተድ) ጋር በማያያዝ የተጠኑ ጥናቶች በርካቶች ሲሆኑ፤ በጉዳዩ ላይ የበለጠ ግንዛቤ ለመያዝ እነሱን ማንበብ ጠቃሚ ነው።)

የሁለቱን ዘመን ለመረዳት «ዘርዓያዕቆብና ወልደ ሕይወት በ17ኛው ክ/ዘ ያገኙት ማህበረሰብ በቁሳዊ ሐብቱ የደኸዬ፣ በዓለማዊ ሕይወቱም እጅግ የተጎሳቆለ ነው፡፡» የሚለውን የብሩህ ዓለምነህን አስተያየት ይዘን፤ ስለቀንዲልነታቸው «የኢትዮጵያ የጽሑፍ ፍልስፍና ከጥበብ (wisdom) ሥራዎች ወደ አመክኖአዊ (rational)፤ ከውርስ ትርጉም ወደ ወጥ (original) ሥራነት ለመሸጋገሩ ህያው ምስክሮች ናቸውና – የዘርዓያዕቆብ (ወርቅዬ) እና የተማሪው የወልደሕይወት (ምትኩ) ሐተታዎች (philosophical treatise) " የሚለውን አስምረንበት ውይይታችንን እንቀጥል፡፡

የዘርዓያዕቆብ ፍልስፍና መሠረት በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥሮ የነበረው የሃይማኖቶች አለመግባባትና ክርክር ነው። ዘርዓያዕቆብ እንደ ፈላስፋ በሃማኖታዊ ሥርዓትና ትምህርት ውስጥ ነው ያደገው። "ሐተታ" በተሰኘ ሥራው ውስጥም ሀሳቡን ሲያዳብር ፈጣሪ የፍልስፍና ጉዞውን እንዲያቀናለት በመጠየቅ ነው። ሐተታ ውስጥ ዘርዓያዕቆብ እንደሚነግረን ሁሉን በፈጠረ ፈጣሪና ለሰው ልጅ ሕገ ልቦና በሰጠ አምላክ ስም በሕይወቴ የገጠሙኝን ነገሮች በዚች መጽሐፌ ውስጥ አቀርባለሁ በማለት ነው።(ፋሲል መርአዊ ሰምነር 1976ን ጠቅሶ እንዳሰፈረው።)ጥናቱ"በመሠረታዊነት ዘርዓያዕቆብ የማህበረሰባዊ ፍትህና የግለሰብ ተፈጥሮ ላይ ሲያተኩር፣ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ደግሞ የመንግሥት አወቃቀርና የሕዝብ አስተዳደር ላይ ለማተኮር ሞክረዋል፡፡" ማለቱንም ልብ ይሏል።

### ስለ ሁለቱ፤

ክለሳ ድርሳናችን እንደሚያመለክተው፣ ካህናቱ መንፈሳዊ ሕይወት (ከተፈጥሮ ሕግ ጋር መስማማት) እና ዓለማዊ ሕይወት ተጫራቾች አለመሆናቸውን በማስተማር ሕዝቡ ከወደቀበት የጉስቁልና ሕይወት እንዲያንሰራራ ማድረግ ይችሉ ነበር።ሆኖም ግን ካህናቱ ይሄንን ነገር ማድረግ ባለመቻላቸው የእነዚህን ሃይማኖታዊ ልሂቃን ሽክም ለመሸከም የመጡት ዘርዓያዕቆብና ወልደ ሕይወት ናቸው።

የአፄ ቴዎድሮስን የዘመናዊነት ፕሮጀክት ሊሸከም የሚችለው ነባሩ ሃይማኖታዊ ትምህርት ሳይሆን የዘርዓያዕቆብና የወልደ ሕይወት የሥነ ሰብዕ ትምህርት ብቻ ነው። የእነዚህ ፈላስፎች የባህልና የእምነት ፍተሻ የአብርሆት ዘመንን በማምጣት በኋላ ላይ አፄ ቴዎድሮስ ላይ ለሚያመረው የዘመናዊነት ፕሮጀክት አስቀድሞ የባህል መደላድል የመፍጠር አቅም ነበረው።በመሆኑም የዘርዓያዕቆብና የወልደ ሕይወት አዲሱና መሠረታዊ ፍልስፍና የሰው ልጅ መንፈሳዊ ከፍታን የሚያመጣው የተደላደለ ቁሳዊ መሠረት ሲኖረው ነው!" የሚል ነው፡፡

ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርዓያዕቆብ "ሐተታ" የተሰኘውን የፍልስፍና መንገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው የሃይማኖት ግጭትና አለመግባባት እንደመፍትሄ አድርጎ ለማስቀመጥ ይጥራል። በዚህ ፍልስፍና ውስ ጥም ከፈጣሪ ህልውና፣ የእውነት ተፈጥሮ፣ በዓለም ላይ ያለውን ግጭትና መንስኤው እና የሥነምግባር ፍል ስፍና ለማዳበር ይሞክራል።

የኢትዮጵያ ፍልስፍና በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ የሚካተት ነው።ይሄንን ዘውግ የመሠረቱት ፈላስፎቻችን ደግሞ ዘርዓያዕቆብና ወልደ ሕይወት ናቸው። (ፍልስፍናንና ሃይማኖትን በማጣመር ለመጀመሪያ ጊዜ ወንበር የዘረጋው ግን ዘርዓያዕቆብ ነው። ለዚህም ነው ወልደ ሕይወት ከሌሎች የአገራችን ሊቃውንቶች ለየት ያለ ሐሳብ ይዞ የመጣው፡፡)

የወልደሕይወት ፍልስፍና የዘርዓያዕቆብ ቅጥያ ነው። ሆኖም ግን ከዘርዓያዕቆብ ወደ ወልደ ሕይወት የተደረገው ሽግግር ዕድገትም ምልሰትም አለው።(ብሩህ ይህንን "ሽግግሩ ዕድገት አለው" የምንለው ከስፋት እና ከአቀራረብ (Scope and method) — ከሚያነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች ብዛት፣ ስፋትና የማስተማር ሥነ ዘዴ አንፃር ሲሆን፤ "ሽግግሩ ምልሰት አለው" የምንለው ደግሞ ከይዘትና ከአዲስነት (Content and originality) — ከርዕሰ ጉዳዮቹ ጥንካሬና ከአዲስነት አንፃር ነው፡፡" በማለት ያብራራዋል።)

ዘርዓያዕቆብ ያላነሳቸው ሆኖም ግን በወልደ ሕይወት ብቻ የተነሱ ሐሳቦችም አሉ። ለምሳሌ:- ስለ ሕፃናት አስተዳደግ፣ ስለ አለባበስ፣ ስለ ፍቺ፣ ስለ ስልጣንና የመንግሥት ሹመት፣ ስለ መላዕክት እንዲሁም ስለ ሴቶች የወሲብ ስሜት እርካታ ፅፏል።(ወልደ ሕይወት ይሄንን የየጓዳችንን ገመና ነው ወደ አደባባይ አውጥቶ እንወያይበት ያለው። ዘርዓያዕቆብ ስለ ሴቶች መብት የተከራከረ ቢሆንም የስሜቷን ነገር ግን ረስቶት ነበረ፤ ይሄንን ክፍተት ያሟላውና የሴቶችን ጥያቄ ምልዑ ያደረገው ወልደ ሕይወት ነው፡፡)

"ቅጥያ ነው" ካለ በኋላ ወልደ ሕይወት ስለ ስልጣንና የመንግሥት ሹመት ማንሳቱ በዘርዓያዕቆብ የተጀመረው የኢትዮጵያ ፍልስፍና ገና የመጀመሪያው ትውልድ ላይ አድማሱን እያሰፋ ከሃይማኖታዊና ከማህበራዊ ትችቶች ወደ ፖለቲካዊ ጉዳዮች የመስፋት አዝማሚያ መጀመሩን የሚያሳይ ነው፡፡

ከርዕሰ ጉዳዮች ስፋትና ብዛት አንፃር ወልደ ሕይወት የዘርዓያዕቆብን ፍልስፍና ይበልጥ አስፋፍቶታል። የሐተታዎቻቸውን የምዕራፍ ብዛት ብንመለከት እንኳን የወልደ ሕይወት መጽሐፍ ከዘርዓያዕቆብ በ20 ምዕራፎች ይበልጣል፤ የዘርዓያዕቆብ ሐተታ 15 ምዕራፎች ሲኖሩት፣ የወልደ ሕይወት ሐተታ ግን 35 ምዕራፎች አሉት። በምዕራፎቹ ብዛት ልክም ወልደ ሕይወት የሚያነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች ሰፊና ብዛት ያላቸው ናቸው።ለምሳሌ ስለ ጤና እንክብካቤ፣ ስለ ሥራና ተግባረዕድ (የእጅ ሙያ)፣ ስለ ጋብቻና ምንኩስና፣ ስለ አመጋገብና ፆም፣ ስለ በይነ ዲሲፕሊን ትምህርቶች አስፈላጊነት (ከአንድ ቀኖናዊ ትምህርት መውጣት እንዳለብን) እንዲሁም እምነትን፣ አፈታሪክንና ልማድን ስለ መፈተሽ ዘርዓያዕቆብ አስቀድሞ የፃፈባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ቢሆኑም ወልደሕይወት ግን ይበልጥ አስፋፍቷቸዋል፡፡

### ወደ ወልደሕይወት እንመለስ፤

በክላውድ ሰምነር አማካኝነት ስለ ወልደሕይወትም ሆነ ስለ"ሀተታ ወልደሕይወት" ሥራው በሚገባ ተብራርቶ ለዓለም ቀርቧል። (ከሰምነር ሥራዎች፣ በተለይም Classical Ethiopian Philosophy የሚለውን ይመለከቷል።)

የ"ፍልስፍና ፩" እና "ፍልስፍና ፪"" መጻሕፍት ደራሲ ብሩህ ዓለምነህ በአንድ ወቅት "የተዘነጋው ወልደ ሕይወት" በሚል ርእስ አዲስ አድማስ ላይ ባስነበበን ጽሑፍ እንደነገረን ከሆነ፤

"-- ወልደ ሕይወት "ሌባና ቀማኛ" የሚለው ፊውዳላዊውን የገባር ሥርዓት ነው።በኢትዮጵያ የልሒቃን ታሪክ ውስጥ የገባሩን ሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ የተቸው ወልደሕይወት ነው - በ17ኛው ክ/ዘመን።ከወልደሕይወት 200 ዓመታት በኋላ የመጡት አፄ ቴዎድሮስ ሰፋፊ የመሬት ይዞታዎችን ለጭሰኞች በማከፋፈል የገባሩን ሕዝብ ሸክም ለማቃለል ሙከራ አድርገው ነበር፡፡--"

የወልደሕይወት አቀራረብ ከመምህሩ ለየት ያለ ሲሆን፤ አቀራረቡን ለየት የሚያደርገው በመጽሐፍ ቅዱስ የሚታወቁ ሐሳቦችን ሲፅፋቸው የአብዛኛዎቹን ማሳመኛቸውን ከእምነት ወደ አመክንዮ እየቀየረ መሆኑ ነው። ይሄም ተግባሩ የሚያስደንቀው ነው፤ እንደ ኦገስቲንና አኳይነስ ትንታኔዎችን የሠሩት በዚህ መልኩ ነበር፡፡

በፍልስፍና ሕይወቱ ወልደሕይወት በሁለት ነገሮች አብዝቶ ይመሰጣል፤ የመጀመሪያው በማስተማር ሥነ ዘዴው ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ፣ ሥራና የእጅ ሙያ ላይ ያለው ፅኑ አቋም ነው። (የመሬት ከበርቴው የጭሰኛውን ጉልበት በሚበዘበዝባት ፊውዳላዊት ኢትዮጵያ፣ የእጅ ሙያ መሰደቢያ በሆነባት ፊውዳላዊት ኢትዮጵያ፣ የጉልበት ሥራ ለመኳንንት ልጆች አይገባም በሚባልባት ፊውዳላዊት ኢትዮጵያ ላይ ወልደ ሕይወት ስለ እጅ ሙያ (በሐተታው ምዕራፍ 18 ላይ) የፃፈው ነገር እጅግ አስደናቂ ነው፡፡) ብሩህ ይህንን የወልደሕይወትን አስተያየት አስመልክተው ሰምነር "በፊውዳላዊት ኢትዮጵያ የሥራ ባህል ላይ የተሰነዘረ አብዮታዊ ሐሳብ" ማለታቸውንም አስፍሯል።

በ"ሌባና ቀማኛ" ሥራው አማካኝነት በዛ (በ17ኛው ክ/ዘ) የገባሩን ሥርዓት ለመጀመሪያ ጊዜ የተቸው ወልደሕይወት ነው።(ከወልደሕይወት 200 ዓመታት በኋላ የመጡት አፄ ቴዎድሮስ ሰፋፊ የመሬት ይዞታዎችን ለጭሰኞች በማከፋፈል የገባሩን ሕዝብ ሸክም ለማቃለል ሙከራ አድርገው ነበር።)

ከወልደ ሕይወት 260 ዓመታት በኋላ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ በ20ኛው ክ/ዘ መጀመሪያ ላይ እነ ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረየሱስ፣ በጅሮንድ ተ/ሐዋርያት ተ/ማርያም እና ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ሲሆኑ፤ የመሬት ጉዳይ አገሪቱ አሁንም ድረስ ልትሻገረው ያልቻለችው መሆኑንና የ1966ቱ "የመሬት ላራሹ" አብዮትም እንዳልፈታው ብሩህ ትዝብቱን ያክልበታል።

በአጠቃላይ፣ ኢትዮጵያ የአዋቂዎች (በአገር በቀሉም በዘመናዊውም) ምድር ነች። (ምናልባት ያ የአዋቂዎች ምድርነቷ እየቀነሰ መጥቷል፤ የዩኒቨርሲቲዎቻችንና ምሩቃኖቻችን ቁጥር እየጨመረ በመጣበት በዚህ ዘመን ጭራሹንም እየመነመነ ... መጣ የሚለው የአስተያየት ሰጪዎች አስተያየት ቆም ካላደረገን በስተቀር) ኢትዮጵያ የአዋቂዎች ምድር ነበረች። ይህ ደግሞ ከራሷም አልፎ ለዓለሙ ሁሉ ተርፎ እንደነበር ማስረጃዎች ሞልተዋል። ከእነዚህ ለዓለም ከተረፉት እውቀቶችና ፍልስፍናዎች መካከል አንዱ ይሄው የወልደሕይወት ፍልስፍና ነውና ባለውለታነቱ ድንበር የለውም። ለዛሬ በዚሁ አበቃን።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## አሰልጣኝ አብርሃም መብራቱ የፊፋ የቴክኒክ ኤክስፐርት ሆነው ተሾሙ

ብርሃን ፈይሳ

የካፍ ኤሊት ኢንስራትክተር አብርሃም መብራቱ የፊፋ የቴክኒክ ኤክስፐርት ሆነው መሾማቸውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አስታወቀ። አሰልጣኙ በዚህ ዘርፍ በመመረጥ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊም ሆነዋል።

የቀድሞ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን(ዋልያዎቹ) አሰልጣኝ እንዲሁም የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን(ካፍ) ኤሊት ኢንስትራክተር አብርሃም መብራቱ የፊፋ የቴክኒክ ኤክስፐርት ሆነው መሾማቸው ተረጋግጧል። በአሁኑ ወቅት የፕሪምየር ሊግ ክለብ የሆነውን ባህርዳር ከተማ እግር ኳስ ክለብ አሰልጣኝ የሆኑት ኢንስትራክተር አብርሃም ፊፋ ለቴክኒክ ኤክስፐርትነት ያቀረባቸውን መመዘኛዎች ማለፍ ችለዋል። በመሆኑም እንደ ሁኔታው በሚታደስ የሁለት ዓመት ኮንትራት የፊፋ የቴክኒክ ኤክስፐርት ሊሆኑ እንደቻሉ የአትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በድረገጹ ያስነበበው።

የካፍ መስራች የሆነችው ኢትዮጵያ እንደቀዳሚነቷ በእግር ኳሱ ያለችበት ደረጃ አርኪ ባይሆንም በተለያዩ ባለሙያዎች ግን መወከሏ አልቀረም። ከእነዚህ ባለሙያዎች መካከል አንዱ የካፍ ኤሊት ኢንስራትክተር አብርሃም መብራቱ ሲሆን፤ አሁን ደግሞ የዓለምን እግር ኳስ በበላይነት በሚመራው ተቋም የማገልገል ዕድል



የፊፋ የቴክኒክ ኤክስፐርት ሆነው የተሾሙት ኢንስትራክተር አብርሃም መብራቱ፤

አግኝተዋል። ይህ ደግሞ በፊፋ በዚህ ዘርፍ የተመረጡ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ኢንስትራክተር አድርጓቸዋል።

ኢንስትራክተር አብርሃም ለቦታው ተመራጭ ያደረጋቸውም በአፍሪካ በኤሊት ኢንስራክተርነት፣ በአፍሪካ ዋንጫ እና መሰል ትልልቅ ውድድሮች በቴክኒክ ጥናት ቡድን አባልነት በሚያደርጉት ተሳትፎ ነው። በተጨማሪም በአሰልጣኝነት በኤዥያ እና የመን እግር ኳስ ላይ ያላቸው የስራ ልምድ እንደሆነም ነው የተጠቀሰው። አሰልጣኙ የፊፋ የቴክኒክ ኤክስፐርት በመሆናቸው ከሚሰጣቸው ተግባራት መካከል፤ በኤሊት የእግር ኳስ አሰልጣኝነት፣ በወጣቶች እግር ኳስ፣ በታዳጊዎች እግር ኳስ፣ ለቴክኒክ ዳይሬክተሮች፣ ለኢንስትራክተሮች እና ከእግር ኳስ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው ጉዳዮች ዙርያ ስልጠናዎች(ኮርሶችን) ማዘጋጀት ይገኝበታል።

በተጨማሪም ለአባል ሀገራት እና አህጉራዊ ኮንፌዴሬሽኖች በእግር ኳስ ልማት ዙርያ የቴክኒክ ማማከር፤ የአባል ሀገራት የእግር ኳስ ልማት ፕሮግራሞች እና ተግባራትን መከታተል፤ አዲሱ የፊፋ ቴክኒክ ልማት ፕሮግራም ዝግጅት እና አስፈላጊ ሰነዶችን በማዘጋጀት ላይ መሳተፍ እንዲሁም ሌሎች በፊፋ የቴክኒክ ልማት መምሪያ ስር የሚሰጣቸው ተግባራትን መከወንም ይጠቀሳሉ።

ኢንስትራክተር አብርሃም የቀድሞው የወንጂ ስኳር እና ጉምሩክ አሰልጣኝ ሆነው ሰርተዋል። ከኢትዮጵያ ባለፈም በየመን ብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝነትና ስኬታቸው ይታወቃሉ። ከ22 እና 23 ዓመት በታች ቡድን አሰልጣኝ እና የየመን እግር ኳስ ማህበር የቴክኒክ ዳይሬክተር በመሆንም ሰርተዋል። ዋናውን የየመን ብሄራዊ ቡድን በመምራትም እአአ በ2019 በተባበሩት አረብ ኤሜሬትስ አዘጋጅነት ለ17ኛ ጊዜ በተካሄደው የእስያ ዋንጫ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለተሳትፎ እንዲበቃ በማድረግ የቻሉ ሲሆን፤ በዚህም ከፍተኛ አድናቆት አግኝተዋል። ይህን ተከትሎም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ብሄራዊ ቡድኑን (ዋሊያዎቹን) እንዲያሰለጥኑ በቀረበላቸው ጥሪ መሰረት ወደ ኢትዮጵያ መመለሳቸው ይታወቃል።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንን በማሰልጠን በቆዩበት ወቅትም ዋልያዎቹ ላለፈው የካሜሩን የአፍሪካ ዋንጫ ከስምንት ዓመት በኋላ ተሳታፊ እንዲሆኑ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ይህም በአፍሪካ ዋንጫው ማጣሪያ ዋልያዎቹን እየመሩ ባህርዳር ስቴድየም ላይ ኮትዲቫርን ሁለት ለአንድ በማሸነፍ ያስመዘገቡት ሦስት ነጥብ ከሚጠቀሱ ስኬቶቻቸው አንዱ ሆኖ ይታወሳል። ይሁንና አሰልጣኙ ከኢትዮጵያ እግር ካስ ፌዴሬሽን ጋር ዋልያዎቹን ለማሰልጠን ከተስማሙበት ከሁለት ዓመት በላይ ቡድኑን ይዘው መቆየት አልቻሉም። ከብሄራዊ ቡድን አሰልጣኝነት ከተነሱ በኋላም የኢትዮጵያ ቤትኪንግ ፕሪምየር ሊግ ተሳታፊ የሆነውን ክለብ ሰበታ ከነማን በማሰልጠን ውጤታማ መሆናቸውም ይታወሳል። አሰልጣኙ በርካታ ክለቦች የሚፈልጓቸው የነበረ ቢሆንም ከሰበታ ከተማ በመልቀቅ የባህርዳር ከተማን ለማሰልጠን በመስማማት አሁንም ድረስ ክለቡን እየመሩ ይገኛሉ።

አሰልጣኙ አሁን ላይ ሀገራቸውን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስጠራት የሚችሉበት እድል አግኝተዋል። ይህንን ተከትሎም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የተሰማውን ደስታ ገልጿል። ኢንስትራክተር አብርሃም መብራቱ በፊፋ በተሰጣቸው አዲሱ ስራቸው ውጤታማ እንዲሆኑም ልባዊ ምኞቱን አስተላልፏል።

## በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ

በከሳሽ አቶ ተስፋ ጌታቸው እና በተከሳሽ አቶ አስቻለው ካሱ መካከል ባለው የቼክ ክስ ክርክር ጉዳይ አመልካች ዓባይ ባንክ አ/ማ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ/ም በመዝገቡ ላይ አቤቱታ ያቀረበ በመሆኑ መዝገቡ መንቀሳቀሱን አውቀው ከሳሽ የሆኑት አቶ ተስፋ ጌታቸው አቤቱታውን ከሀዋሳ ከተማ ታቦር ክ/ከተማ ዱሜ ቀበሌ ሊቀመንበር በመቀበል ለአቤቱታው ያሎትን መልስ ለ7/02/2015 ዓ/ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ሀዋሳ ማዕከል እንዲቀርቡ ሆኖ በቀጠሮ ዕለት ሳይቀርቡ ቢቀሩ ፍ/ቤቱ መቅረብ እንዳልፈለጉ በመቁጠር መዝገቡ በሌሉበት አይቶ የሚወሰን መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሀዋሳ ማዕከል ቁ.1**

በከሳሽ አቶ አንዱዓለም ግዛው እና በተከሳሽ አቶ አስቻለው ካሱ መካከል ባለው የቼክ ክስ ክርክር ጉዳይ አመልካች ዓባይ ባንክ አ/ማ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ/ም በመዝገቡ ላይ አቤቱታ ያቀረበ በመሆኑ መዝገቡ መንቀሳቀሱን አውቀው ከሳሽ የሆኑት አቶ አንዱዓለም ግዛው አቤቱታውን ከሀዋሳ ከተማ ታቦር ክ/ከተማ ዱሜ ቀበሌ ሊቀመንበር በመቀበል ለአቤቱታው ያሎትን መልስ ለ7/02/2015 ዓ/ም 3፡30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ሀዋሳ ማዕከል እንዲቀርቡ ሆኖ በቀጠሮ ዕለት ሳይቀርቡ ቢቀሩ ፍ/ቤቱ መቅረብ እንዳልፈለጉ በመቁጠር መዝገቡ በሌሉበት አይቶ የሚወሰን መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሀዋሳ ማዕከል ቁ.1**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም እታለም ትሬዲንግ አክሲዮን ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-A14013 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5BLSF2MN944362 ሞዴል ZZ12575434IW የሞተር ቁጥር WD615472II007025227 የሊብሬ ቁጥር 0278100 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 30/12/2014 አመልክተዋል፡ ፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጂ ኤስ ዋይ ዲ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-27876 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር JTFDE626540108361 ሞዴል LN166L-PRMDSW የሞተር ቁጥር 3L-5358798 የሊብሬ ቁጥር 374949 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 30/12/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መኑን እንገልፃለን

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ደገፈ ወልዴ ኤዳሞ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-82672 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5BLNF1FA105017 ሞዴል ZZ1257S4341W የሞተር ቁጥር WD615 47*151207020567 የሊብሬ ቁጥር 0162310 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 30/12/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሱራፌል በቀለ ደግፌ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B05958 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር JTMHV05J704281485 ሞዴል VDJ200L-GNTEZW.የሞተር ቁጥር 1VD 0484709 የሊብሬ ቁጥር 198868/238896 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 1/13/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ማክሮ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭና ትሬዲንግ ሀ/የተ/የግ/ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-93369 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELND87D250027 ሞዴል ZZ3257N3647A የሞተር ቁጥር WD615.69*161217024077* የሊብሬ ቁጥር 0191337 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 1/13/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ማክሮ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ እና ትሬዲንግ ሀ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-91247 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELND5GD222024 ሞዴል ZZ3257N3647A የሞተር ቁጥር WD615.69*161117030207* የሊብሬ ቁጥር 0188138 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 1/13/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥመሆኑን እንገልፃለን፡፡

**አዲስ ኣበባ ከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ አሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ